

# ትንሣኤ



በጋሞ ጎፋ ሀ/ስብከት በጋሞ አውራጃ በጨንቻ ወረዳ የምትገኘው የብርብር ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፸፫

ሚያዝያ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም

ዋጋ ፩ ብር

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

ዋና አዘጋጅ ቀ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ
ም/ አዘጋጅ መ/ ክነሬ. ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማውጫ

**ገጽ**

## አርእስት

ደብዳቤዎች ............ ፩
(ርእስ አንቀጽ) ትምህርት የዕውቀት መፍለቂያ
ምንጭ ነው ............ ፪
የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጉብኝት
በጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት ............ ፬
ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ............ ፲
ዜና ሊቃውንት ............ ፲፪
የብርብር ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ ............ ፲፫
ዜና እረፍት የሠዓሊ ሙሉጌታ ዕንግዳ አጭር
የሕይወት ታሪክ ............ ፲፬
ልማት በቤተ ክርስቲያን ............ ፲፭
ስብከተ ወንጌል ............ ፲፯
የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ............ ፲፰
መድኀኒ ዓለም ............ ፳
ከቋጥኝ የተሠራው የኮሬብ ቤተ መቅደስ ታሪክ ............ ፳፩
ማኅበራዊ ኑሮአችን ............ ፳፪
የዐለም አብያተ ክርስቲያናት ስለሰብአዊ መብት ............ ፳፫

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ በክርስቶስ ስም ሰላምታ አቀርባለሁ ከሰላምታዬ ቀጥዬ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሳቀርብ የማያዳግም መልስ እንደማገኝ በመተማመን ነው ።

፩ኛ/ የሐ ሥራ ፩.፲፰—፳ ያለው ቃል አሳልፎ የሰጠውን የይሁዳን ሞት በግንባሩ ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰንጥቆ አንጀቱ ሁሉ ተዘረገፈ ሲል የአሟሟቱን ሁኔታ ሲገልጽ ሌላው ደግሞ በማቴ ፳፯.፫—፮ ያለው ዓረፍተ ነገር "አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ ሰላሳውንም ብር መልሶ በአቴናው ላይ ከወረወረ በኋላ ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ በማለት ታንቆ ሞተ ሲል የአሟሟቱን ሁኔታ ይናገራል ፤ ስለዚህ የይሁዳ አሟሟት እንዴት እንደሆነ በማያሻማ መንገድ ትገልጹልኝ ዘንድ በትሕትና እጠይቃለሁ ።

፪ኛ/ በማቴ ወን ፳፫.፰—፲፪ ያለውን ቃል ስንመለከት "መምህር ተብላችሁ አትጠሩ መምህራችሁ አንድ የሰማይ አባታችሁ ነውና ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ ሊቃችሁ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና" ሲል በእነዚህ ስሞች እንዳንጠራ ይከለክለናል ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ስያሜዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ውስጥ አገልጋይ የሆኑት ካህናት የሚጠሩበት ስም ሆኖ እናገኘዋለን ታዲያ እንደመጽሐፍ ምሥጢር ትክክለኛ አባባል ከሆነ ሕጉን መጣሳችን አይሆንም ወይ?

ትርጓሜያቸውን ተንትናችሁ እባካችሁ አስረዱኝ ።
ዲ/ዓይናለም አማረ
አሰቦት ደብረ ወገግ ገዳም

መልስ ፤

ዲያቆን ዓይናለም አማረ ስላቀረብክልን ሰላምታ እያመሰገን ለአቀረብካቸው ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን በመጀመሪያ ጥያቄህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክረስቶስ ስለአስያዘው ይሁዳ አሟሟት እንድናስረዳህ ጠይቀሃል እኛም ከቅዱሳት መጻህፍት ተመልክተን ከአባቶችም ሊቃውንት ጠይቀን መልሱን አቅርበንልሃል ።

ይሁዳ ከክርስቶስ ፲፪ ደቀመዛሙርት መካከል አንዱ ስለነበር ከጌታ አይለይም ነበር አይሁድ ክርስቶስን እንይዘዋለን ብለው ሲሄዱ በተአምራት ሲያመልጥ ያየው ነበር እርሱም እንደልማዱ በተአምራቱ ያመልጣል እኔም ወርቁን እንደያዝኩኝ እቀራለሁ ብሎ ፴ ብር ተቀብሎ አስይዟቸዋል ይሙት በቃ እንደተፈረደበት ባየ ጊዜ ንጹሕ ሰው ያስገደልኩኝ ንጹሕ ደም ያፈሰስኩኝ አላበጀሁም በደልሁ ብሎ ሰላሳውን ብር ይዞ ሂዶ አይሁድን ተቀበሉኝ አላቸው ሚ ላዕሌና ለሊከ አእምር" አንድ ጊዜ የወደድከውን ሰጥተንሃል አንተም የወደድነውን ሰጥተኸናል ።

እንግዲህ እኛ ከአንተ አንተ ከእኛ ምን አለህ? አንተ ለራስሕ እወቅ አሉት "ወገደፈ ውእተ ብሩረ ውስተ ምኩራብ ተአንተ ወሞተ" ይላል ፴ውን ብር ከዕቃ ቤቱ አፍስሶ ገመድ ይዞ ሂዶ ሊታነቅ ገመዱን ከዛፍ አሠረ ዛፊቱ እንደሰው አፍ አውጥታ "አይሁዳ ነስሕ ከመ እሁከ ጴጥሮስ ንስሐ ግባ አለችው።

እርሱም ያልኋትን ትታ ትቀባጥራለች ብሎ እንደገና ከሌላይቱ ዕፅ ገመዱን አሠረ እርሷም ንስሐ ግባ አለችው ፤ ቀባጣሪ ዕፅ ብሎ ሂዶ በቀትር ጊዜ ዕፀዋት ሁሉ አድንኖ አድርገዋል አንሥታ ከምድር ፈጨችው ደም ከልቡ ላይ ወድቆ ሲንፈራገጥ ነጋድያን አልፈው ሲሄዱ አይተው ለዘመዶቹ ያከፋ ዘመዳችሁ ወድቆ ይንፈራገጥላችኋል ብለው ነገሯቸው ተሸክመው ወስደውታል (ወቀቢዎ ነቅዓ አማዕከሉ) ይላል እስከ አርባ ቀን አብጦ ተነፋፍቶ ኑሯል በአርባ ቀኑ ጌታ ባረገ ጊዜ ያ ያሰቀልከው ኢየሱስ አረገልህ ብለው ነገሩት እያለሁ ብሎ ሲወጣ መድረኩ ቢያንቀፈው ሲወድቅ የማንቃው ወንዴ መወርወርያውም ይላል ጎደኑን ቀደደውና ንዋየ ውስጡ ፈሶ ሙቷል ።

በተጨማሪም እያለሁ ብሎ ሲወጣ መላእክት ሐፀ እሳት ኩናተ እሳት ይዘው ታዩት ወደ አልጋው ሸሸቼ እገባለሁ ሲል የአልጋው ጠገግ ጎኑን ስለቀደደው ንዋየ ውስጡ ፈሶ ሙቷል ።

እንግዲህ የይሁዳ አሟሟት ይህንን በመሰለ አስከፊ ሁኔታ ስለሆነ ጠያቂው በመልሳችን እንደምትረካ ተስፋ እናደርጋለን ።

ሁለተኛ ጥያቄህ ደግሞ መምህራን ተብላችሁ አትጠሩ እንዲሁም ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ ይላል ይህ ትክክል ነው ከተባለ ለምን የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ይጠሩበታል የሚል ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መምራን ተብላችሁ አትጠሩ ሊቃውንትም ተብላችሁ አትጠሩ መምህራችሁም አለቃችሁም አንድ ክርስቶስ ነውና ማለቱ በስሙ አትጠሩ ማለቱ ሳይሆን ፈጣሪያችሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ የሚሉ መምህራንና አለቆች አይኑሮችሁ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣዖት ስገድ እያሉ ከሚያስተምሩ መምህራንም ተምራችሁ መምህራን አለቆች እየተባላችሁ ልትጠሩ አይገባችሁም ማለቱ ነው እንጂ መምህራን ሊቃውንት ተብሎ መጠራትን መከልከሉ (መንቀፉ) አይደለም ይህንንም በመመልከት ቅድስት ቤተክርስቲያናችን እጅግ በጣም የተማሩትን ምሁራን ሊቃውንት እያለች ትጠራቸዋለች ።

ይህም ሕግንና ሥርዓትን መጠበቅ እንጂ ማፍረስ እንዳልሆነ ሁሉም እንባብያን ሊያውቁትና ሊረዱት ይገባል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርት የዕውቀት መፍለቂያ ምንጭነው

ገለባውን ከፍሬው ለመለየት ነፋስ አስፈላጊ እንደሆነ ክፉውን ነገር ከመልካም ለይቶ ለማወቅ ትምህርት ፍቱን መሣሪያ ነው ። አባቶች የትምህርትን ጠቃሚነት በመረዳት "ካልተማሩ አያውቁ ካላወቁ አይጸድቁ" ይላሉ ።

የትምህርትን ጠቃሚነት ቀደም አድርጋ የተገነዘበችው ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ቀለም በጥብጣ ብዕርን ቀርፃ ማስተማር ከጀመረች ብዙ ዓመታት አልፈዋል ትምህርቱንም በምታስተምርበት ጊዜ የቦታ ምርጫ አታደርግም ፡ በየደጁ ሰላሙ በየመቃብር ቤቱ በየታዛው በየዛፉ ሥር ሁሉ ታስተምራለች ፤ ከዚህ ሌላ ሰዎች በርከት ብለው በሚገኙበት ቦታ በመገኘት ከማስተማር ተግባር ተቆጥባ አታውቅም ።

በሌላ በኩል ደግሞ በታላላቅ አድባራትና ገዳማት የአብነት መምህራንን እየመደበች ጠለቅ ያለ ትምህርት በማስተማር እነርሱን የመሳሰሉ መምህራንን እያስተማሩና እያሠለጠኑ በተፈላጊ ቦታ እንዲመደቡ ለማድረግ ባላት አቅም ትጥራለች ።

ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ የምታደርገው የትምህርት እንቅስቃሴ ወቅቱን የተከተለ እንዲሆን ብዙ ጥረት እያደረገች ናት ጊዜውን ተከትለው የሚሠሩና የሚያሠሩ ተወዳጅ አባት ብፁዕ ወቅዱስ አብነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ዋና ሥራ አሥኪያጅ ስላሏት ቅድስት ቤተክርስቲያናችን የምታሳየው የሥራ እንቅስቃሴና ቅልጥፍና ከምንጊዜውም የላቀ ነው ።

የመምህራን እንክብካቤ እንዲደረግ ቅዱስነታቸው ደጋግመው በሰጡት መንፈሳዊ መመሪያ መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ ከፓትርያርኩ ገቢ ገንዘብ በሚከፈል ደመወዝ ዓራቱን ጉባኤ የሚወክሉ አንድ መምህር እንዲቀጠሩ ሲደረግ ከእርሳቸው ለሚማሩ ተማሮችም ለቀለብና ለልብስ የሚሆን ገንዘብ እንዲሰጣቸው ቅዱስነታቸው ስለፈቀዱ መምህሩ በቅዱስ ጳወሎስ ት ቤት በማስተማር ተማሮቹ በመማር የሚያሳዩት ትጋት እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው ።

በየአህጉረ ስብከቱም ፮ የካህናት ማሰልጠኛዎች ስለተከፈቱ ካህናቱ በየአራት ወራቱ እየተመረቁ በመውጣት ጠንክረው በማስተማር ላይ ስለሚገኙ የካህናቱ ኑሮ እየተሻሻለ ፤ የሚሰጡትም መንፈሳዊ አገልግሎት እየተሟላ በመሄድ በቤተ ክርስቲያናችን የነበረው የዕውቀት ጭራ በበለጠ እየበራ ቶው ለማለት ያስደፍራል ይህ ሁሉ የሚያስረዳው የቤተ ክርስቲያናችን የትምህርት እንቅስቃሴ እየተጠናከረ መሄዱን ነው።

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በ፭ኛው አጠቃላይ የመንበረ ፓትርያርክ መ/ጉባኤ በሰጡት መመሪያ ላይ እስከ ዛሬ በ፮ አህጉረ ስብከት ፮ የካህናት ማሠልጠኛ ተቋቁመው ሥራቸውን በማጠናከር ላይ ይገኛሉ ቤተ ክርስቲያናችን በእነዚህ በተቋቋሙት ማሠልጠኛዎች ብቻ ተወስና የምትቀር አይደለችም ወደ ፊት እየተጠና አመች ሆኖ በተገኘበት ሀ ስብከት የካህናት ማሠልጠኛ ይከፈታል ካሉ በኋላ ለማሠልጠንም ሆነ ለመሠልጠን በቂ ገንዘብ ያስፈልጋል ይህም ገንዘብ ሊገኝ የሚችለው በሰበካ ጉባኤ አማካይነት ከምእመናን ነውና የሁላችንም ትምህርት ማተኮር ያለበት የሰበካ ጉባኤን ከማጠናከሩ ላይ ነው ። ሰበካ ጉባኤም ሊጠናከር የሚችለው በትምህርተ ወንጌል ስለሆነ ሁሉም ጠንክሮ እንዲያስተምር በጥብቅ አሳስበው ነበር።

ከዚያ ወዲህ ከየማሠልጠኛዎች ተመርቀው የሚወጡት ካህናትም ሆኑ የአብነት መምህራን ጠንክረው በማስተማር ላይ መሆናቸው ታውቋል ።

ከስድስቱ ማሠልጠኛዎች አንዱ በጋሞ ጎፋ ሀ/ስብከት በሚገኘው ጨንቻ መድኃኔ ዓለም ማሠልጠኛ ሥራውን ከጀመረ ፲ ዓመት ሆኖታል ፡ ቀደም ሲል የሚረዳው በውጪ ሀገር ድርጅት ነበር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከበጎ አድራጊው ድርጅት የሚመጣው የርዳታ ገንዘብ በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ በኩል እየተሰጠ ማሠልጠኛው እንደሌሎች ማሠልጠኛዎች እኩል እንዲካፈል ተደርጓል ።

በዚህ አጋጣሚ ለመጀመሪያ ጊዜ የርዳታ ዕጃቸውን ለዘረጉትና አሁንም ቢሆን ማዕከላዊ አሠራርን ጠብቆ ለሚያከፋፍለው ለልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ለሚለግሱት ምስጋና ይገባቸዋል ።

በጨንቻው ካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት ሁለት የአሠራር ክፍሎች አሉት ፤ አንደኛው አሠራር ከ፬ አውራጃዎች የተመረጡ ፲ ዲያቆናትን ለ፬ ዓመት አሠልጥኖ የሚያስመርቅ ሲሆን ሁለተኛው አሠራር ደግሞ ከየአውራጃው ካህናትን እየመረጠ ለተወሰነ ጊዜ እያሠለጠነ ጠንክረው እንዲያስተምሩ ማድረግ ነው ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከየካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ·ም እስከ የካቲት ፲፩ ቀን ፸፱ ዓ·ም· ድረስ የጋሞ ጎፋን ሀ/ስብከት በይፋ በጎበኙበት ጊዜ ለ፰ ወራት ለሠለጠኑ ፲፮ ካህናት የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል ቅዱስነታቸው የምሥክር ወረቀቱን ከሰጡ በኋላ ባስተላለፉት መንፈሳዊ መልዕክት ትምህርት ሁል ጊዜ የማይቋረጥ የዕውቀት መፍለቂያ ምንጭ ነው ራስ አውቆ ላላወቀው ማሳወቅ ተምሮ ማስተማር ይገባል ትምህርት የሚጠቀመው ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ አይደለም ለሥጋዊም ተግባር ጠቃሚ ነው በሥጋዊ አስተዳደር በኩል የተማረ ሰው ብዙ ሥራዎችን መሥራት ይችላል። በሰማይ የሚበሩት በምድር የሚሽከረከሩት በባህር ላይ የሚንሳፈፉት በጠቅላላ የሰው ልጅ የሚገለገልባቸው መሣሪያዎች ሁሉ የተፈለሰፉትና የተሠሩት በተማሩት ሰዎች ነው ።

አሁን እኛ ስናያቸው የተደከመባቸው አይመስሉን ይሆናል ግን ሳይደክሙ ሳይማሩ ለራስም ሆነ ለወገን የሚጠቅም ዕውቀትን ለማግኘት አይቻልም ካሉ በኋላ ቅዱስነታቸው ወደ መንፈሳዊ ተግባር መለስ ብለው ሲገልጹ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ሲል የሠራውን የቸርነት ሥራ ስለሰው ፍቅርም የተቀበለውን መከራ ለማወቅ የሚቻለው በትምህርት ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ገበሬ ዘሩን ዝም ብሎ በጎተራ ቢያስቀምጠው ሊጨመርና ሊበዛ አይችልም ቢዘራው ግን ይበዛል ከዚያም በኋላ ከራሱ አልፎ ለሌላም ይጠቅማል ፡ ትምህርትም በዘር ይመሰላል ቢያስተምሩበት ወገንን ፡ ሀገርን ራስን ይጠቅማል ከእግዚአብሔርም ዘንድ ከፍ ያለ ዋጋን ይሰጣል ትምህርትን አውቆ ባያስተምሩበት ደግሞ "ግብር ሐካይ ለምንት ኢይግባዕከ ወርቅየ" አንተ ሰነፍ ባሪያ ለምን ወርቄን ቀበርከው ተብሎ ወደ ጨለማ እንደገባው አገልጋይ ከእግዚአብሔር ከፉን ፍርድ አስፈርዶ ወደ ገሃነመ እሳት ያስገባል ከዚህ ስቃይ ለመዳን የተማራችሁትን መልሳችሁ ላልተማሩት ወገኖቻችን እንድታስተምሩ አደራ እንላለን በማለት ቅዱስነታቸው መመሪያ ሰጥተዋል።

ቅዱስነታቸው እንደተናገሩት የተማረ ሁሉ ለራሱ ብቻ እንደጋን ውስጥ መብራተ ሆኖ መቀመጥ አይኖርበትም በድንቁርና ጨለማ የተቀመጡ ወገኖቹን አስተምሮ ወደ እውነተኛው ብርሃን ወደ ክርስቶስ ማቅረብ ይኖርበታል።

ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ብሎ እንዳስተማረው የክርስቶስን ቃል የሚሰማና በሕጉ የሚመራ ሁሉ የዓለም ብርሃን እንደተባሉት ሐዋርያት ያለ ክብርን ይጎናፀፋል ተምሮ የማያስተምር ግን ከላይ በቅዱስ ፓትርያርኩ ቃል እንደተነገረው እንደማይጨምር ዘር በመሆን ይኖራልና የተማረ ሁሉ ነቅቶና ተግቶ ማስተማር ይገባዋል ።

ነቢዩ ዳንኤል ስለ መምህራን ክበር በትንቢቱ ሲገልጽ በምድር ላይ ያንቀላፉ ብዙ ሰዎች ይነቃሉ እኩሌቶቹም ወደ ዘለዓለም ሕይወት ሌሎችም ወደስድብና ወደ ዘለዓለም ኀፍረት ይልና መምህራን የሆኑ ግን እንደሰማይ ፀዳል ይደምቃሉ ለብዙ ሰዎችም ጽድቅን የሚያስተምሩ እንደከዋክብት ለዘለዓለም ያበራሉ" በማለት ተናግሯል ትን ዳን. ፲፪.፪—፫

እንግዲህ በዚህ ዓለም በንቃትና በትጋት በተማረው ትምህርት ያልተማሩትን አስተምሮ አሳውቆ በሚቀጥለው ዓለም በተድላና በደስታ መኖር የሚሹ ምሁራን ሁሉ መሥራት የሚችሉት ብርሃን ዕድሚያቸው በሞት ጥላ ሳይከለል ነው ክብር የክብር ክብርን ለመቀዳጀት እንዲችሉ ያልተማሩትን ጠንክረው ያስተምሩ ዘንድ መንፈሳዊ መልእክቶቻችን ከማስተላለፍ አንቆጠብም ።



www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጉብኝት በጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከየካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም እስከ የካቲት ፲ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ድረስ የጋሞ ጎፋን ሀ/ስብከት ጎብኝተዋል ።

ቅዱስነታቸው ብፁዕ አቡነ ገሪማን በኢትዮጵያ ኦረቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሱዳን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተጠባባቂ ዋና ጸሐፊን ፡ ብፁዕ አቡነ ናትናኤልን የአርሲ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስን ፡ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕን ሊቀ ጳጳስ ፡ የመንፈሳዊ ፍርድ ቤት ኃላፊን እንዲሁም ሌሎችን የክብር ተከታዮች በማስከተል ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ሲነሡ ፡ የመንበረ ፓትርያርክ ልዩ ጸሐፊ ሊቀ ሥልጣናት ኤልያስ አበበ ፡ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘርይሁን የውጭ ሀገር አብያተ ክርስቲያናት ግኑኝነት መምሪያ ኃላፊ አቶ ዘመድኩን ብዙ ወርቅ ሸኝተዋቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን ፩ ሰዓት ከ፲፯ ደቂቃ በአየር ጉዞ በረራ ካደረጉ በኋላ የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ስድስት ሰዓት ተኩል ሲሆን ዓርባ ምንጭ ደርሰዋል ፡ ከዚያም እንደደረሱ ፡ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የሀገረ ስበከቱ ሊቀ ጳጳስ ጓድ ደምፀ ገብረ መድኅን የክፍለ ሀገሩ ምክትል አስተዳዳሪ ሌሎችም የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች የሀ/ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አለቃ መኮንን ካህናት የሰበካ ጉባኤ አባላት የሰንበት ት/ቤት ተማሮች በርከት ያሉ ምዕመናንና ምእመናት እንኳን ደህና መጡልን በማለት ተቀብለዋቸዋል ፡ ፫ ሕፃናትም ዕቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ።

በአየር ማረፊያ የሚደረገው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ቅዱስነታቸው ወደ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በማምራት ከቤተክርስቲያኑ ሲደርሱ በዚያ ተሰልፎ ይጠባበቅ የነበረው ሕዝበ ክርስቲያን በልልታና በጭብጨባ ሲቀበላቸው የሰንበት ተማሮችም ከበሮ ይዘው እየዘመሩ ተቀብለዋቸዋል። ሕፃናትም ዕቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ገብተው ጸሎት ካደረጉ በኋላ ለመቀበያ በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር እንደተቀመጡ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የክፍለ ሀገሩ ሊቀ ጳጳስ እንኳን ደኅና መጡ በማለት አጠር ያለ ንግግር ካረጉ በኋላ ቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ወደ መንበረ ጵጵስናው መንገዳቸውን በመቀጠል በዚያ አዳር ሆኗል ።

የካቲት ፰ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ላይ ከክብር ተከታዎቻቸው ጋር በመሆን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ልብሰ ተክህኖ የለበሱና መስቀል ጽንሐሕ የያዙ ቀሳውስትና ዲያቆናት የሰንበት ተማሮች የሰበካ ጉባኤ አባላት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ምእመናን በመዝሙር በልልታና በጭብጨባ ተቀበሏቸው ፡ ቅዱስነታቸውም ለመቀበል በግራና ቀኝ ተሰልፎ የቆመውን ሕዝበ ክርስቲያን በመስቀላቸው እየባረኩ ወደ ቤተ መቅደሱ እንደገቡ ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሯል ጸሎተ ቅዳሴውም የተመራው ፡ በቅዱስነታቸውና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ነበር ።

ጸሎተ ቅዳሴው ጧት በ፪ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ እንዳበቃ ከስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ የተላኩ ሰባኪያን ትምህርተ ወንጌል ሰጥተዋል ፡ ለሦስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለመቀበያ በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር ላይ እንደተገኙ መዘምራን ፡ "ፀሐይ ብሩህ ወወርህ ንፁሕ ተክለ ሃይማኖት ሣህልክ ይርከበነ" ወደ አማርኛ ሲተረጐም እንደ ፀሐይ የምታበራ እንደ ጨረቃ የምትደምቅ አባታችን ተክለ ሃይማኖት ሆይ ይቅርታህ ይደረግልን ፡ ማለት ነው ካህናቱ ይህን አለዝበው ለ፳ ደቂቃ ያህል አሸበሸቡ ፤ የሰንበት ተማሮችም "ሐዲስ ሐዋርያ ተክለ ሃይማኖት ሐዐነቶ ገዳም ወአልሐቆቶ ጸሎት ለተክለ ሃይማኖት የሚል ግሥ ገሥው እጅግ በሚያስደስትና መንፈስን በሚመስጥ ዜማ አሸብሽበዋል ቀጥሎም የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ስለቅዱስነታቸው መንፈሳዊ ጉብኝት የተሰማቸውን ደስታ በአጭሩ ገልፀዋል ብፁዕነታቸው ባደረጉት ንግግር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ደክመኝ ሰለቸኝ የማይሉ የተቸገረውን ለመርዳት ያዘነውን ለማጽናናት የደከመውን ለማበርታት የሚያደርጉት ጥረት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ትልቅ ፀጋ መሆኑን ገልፀው ቅዱስ ኤፍሬም "ወኩሉ ፍጥረት ተፈሥሐ በምጽዓትከ" በመምጣትህ ፍጥረቱን ሁሉ ደስ አለው ብሎ እንደተናገረው በቀድስነትዎ መምጣት ያልተደሰተ ምዕመን አይገኝም ሁሉም ተደስቷል ካሉ በኋላ ።

ይህ ሀ/ስብከት እስከ አሁን ድረስ በፓትርያርክ የመጎብኘት ዕድል አልገጠመውም ነበር ቅዱስነትዎ ለዚህ ታላቅና ወደር የማይገኝለት ዕድል ስላበቃልን ፡ ለደስታችን ወሰን የለውም ብለዋል ብፁዕነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል ፡ በቅዱስነትዎ ዘመነ ሢመት ብዙ የሚያስደንቁ የመንፈሳዊያን ሥራዎች ተሠርተዋል እየተሠሩም ናቸው በማለት በቅዱስነታቸው መዋዕለ ሢመት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተሠሩትን ታላላቅ ሥራዎች ለማስረጃ ያህል አልፈው አለፈው ጠቅሰው ለቅዱስነታቸው ዕድሜና ጤና በመመኘት ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ቀጥሎም ፀሎተ ወንጌል ተጀምሮ "እስመ መምህረ ሕግ ይሁብ በረከተ" የሚለው መዝሙረ ዳዊት ተሰብኮ ሲያበቃ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የዮሐ ወንጌል ፲.፩–፲፰ አንብበው መንፈሳዊ መመሪያና ትምህርት ሰጥተዋል ቅዱስነታቸውም የሰጡት መመሪያና ትምህርት የሚከተለው ነው።

ይህ ሀ/ስብከት ዳር ሀገር እየተባለ ሲጠራ ሰምተን ነበር እንደተመለከትነው ግን ዳር ሳይሆን መካከል ሆኖ



ቅዱስነታቸው ለመቀበል የተሰበሰበውን ሕዝብ ሲባርኩ

አግኝተነዋል ትናንት በአየር ማረፊያ ዛሬ ደግሞ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ስለአደረጋችሁልን አቀባበል በጣም ደስ ብሎናል ፡ ከሌሊት ጀምራችሁ እስከአሁን ድረስ ያደረጋችሁት መንፈሳዊ አገልግሎት የሚመሰገንና ከእግዚአብሔርም ዘንድ ከፍ ያለ ዋጋን የሚያሰጥ ነው።

ዓርባ ምንጭ በሀገራችን ከፍ ያለ ቦታ ነው ዛሬ አዲስ ስለሆነ ጥቅሙ ገና ጎልቶ አልታወቀም ወደፊት ግን እጅግ በጣም ጠቃሚ እንደሚሆን አያጠራጥርም በዚህ ቦታ ለታነፀው ቤተ ክርስቲያን እስከ ዛሬ ስም አልሰጠነውም ነገር ግን ከዛሬ ጀምሮ ይህ ደብር ደብረ መድኃኒት ይባላል ይህንኑ ደብር የሚያስተዳድረውም መልአከ ሰላም ይባላል ። ቤተ ክርስቲያኑን የሚያገለግሉ ምሁራን ርእስ ፣ ደብር ፣ ሊቀ ጠበብት ፣ ቀኝ ጌታ፣ ግራ ጌታ ፡ እየተባሉ ይሾሙበታል በማለት ቅዱስነታቸው መንፈሳዊ መመሪያ ሰጥተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መንፈሳዊ መልእክታቸውን በመቀጠል አሁን እኛ ትምህርት የምንሰጣችሁ አስተማሪ የሌላችሁ ሁናችሁ አይደለም ጥሩ አስተማሪ ጥሩ ኃላፊ አሏችሁ እርሳቸው በንቃትና በትጋት እንደሚያስተምሯችሁ የታወቀ ነው ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ለጵጵስና የተመረጡት በወሊጋ ሀ/ስብከት በማስተማር ላይ እንዳሉ ነው ፡ ከተሾሙ በኋላ ወደዚህ ሀ/ስብከት ተመድበው ሲመጡ የወሊጋ ሕዝበ ክርስቲያን ወደሌላ ሀ/ስብከት ለምን ይሄድብናል በማለት ተቃውሞ ነበረ ። ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ስለሆነ በዚሁ ፀንተዋል ።

እንዲሁም በመዝሙራቸው በአቀባበላቸው ከሌላው የበለጡ የሰንበት ተማሮችም በዚህ ሀ/ስብከት ተመልክተናል። ይህ ሁሉ የብፁዕነታቸው የሥራ ፍሬ ነው ካሉ በኋላ ቅድስነታቸው ዮሐ ፲.፳፯ ሉቃስ ፯.፴፮ የሚገኘውን በመጥቀስ በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ እንዳለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክረስቶስ እናንተም ከዚህ ቤተ ክርስቲያን የተሰበሰባችሁት የክርስቶስን ቃል ሰምታችሁ ነው ይህንንም ማወቅ ተገቢ ነው ክርስቶስ በጐቼን አውቃቸዋለሁ እነርሱም ይከተሉኛል ፤ እኔም የዘለዓለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ ብሏል በክርስቶስ ያመነ ምንጊዜም ከመከራ ሥጋና ከመከራ ነፍስ ይድናል ሁልጊዜ ድምፁን እየሰማን ልናገለግለው ይገባናል የበጐች ምእመናን አምላክ ለእኛ ያደረገልንን ውለታ ካወቅንና ከተረዳን ሕያዋን ሆነን እንኖራለን የእግዚአብሔርም ጸጋ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ይኖራል ክርስቶስ ሰው ሆኖ ያስተምር በት በነበረው ዘመን ስምዖን ፈሪሳዊው ጋበዘው ፡ ወደዚሁ ሰው ቤት ገብቶ ሳለ አንዲት ኃጢአተኛ ሴት ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ አምጥታ እያለቀሰች በእንባዋ ጭምር ታርሰው ጀመረች በራስ ጠጉሯም እግሩን እያበሰች ትስመው ሽቱም ትቀባው ነበር ።

ፈሪሳዊው ስምዖን ይህንን በተመለከተ ጊዜ አምላክማ ቢሆን የዳሰሰችው ሴት ኃጢአተኛ እንደሆነች ባውቅም ነበር ሲል የጥርጥር ቃል ተናገረ ክርስቶስም የስምዖንን መጠራጠር አውቆ የሚከተለውን ማስረጃ አቀረበለት "አንድ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት ለአንዱ ፭፻ ዲናር ነበረበት ለሁለተኛው ፶ ነበረበት ሁለቱም የሚከፍሉት ስለአጡ አበዳሪው ተወላቸው እንግዲህ ከእነርሱ አብልጦ የሚወደው ማንኛው ነው ? አለው ስምዖን መልሶ ብዙ የተወለት ነው ስላለው ስምዖን ሆይ ! እውነት ፈረድክ ካለ በኋላ ወደ ሴቲቱ መለስ ብሎ ይህችን ሴት ታያታለህን? እኔ ወደ ቤትህ ገባሁ ለእግሬ ውኃ እንኳን አላቀ





www.ethiopianorthodox.org

ረብክልኝም እርሷ ግን በእንባዋ እግሬን አራሰች በጠጉሯም አበሰች አንተ ራሴን ዘይት አልቀባኸኝም እርሷ ግን እግሬን ሽቱ ቀባች ካለ በኋላ ኃጢአቷን ፍቆ ወደፊት ኃጢአት እንዳትሠራ በማስጠንቀቅ አሰናብቷታል ። ሁልጊዜ ማሰብ ያለብን እግዚአብሔር ለኛ ያደረገልንን ይቅርታና ቸርነት ነው ፤ ወደ እግዚአብሔር ከተመለስን በደላችን ሁሉ ይፋቅልናል ካሉ በኋላ ልጆቸ እሁድ እሁድ ወደ ሰንበት ት/ቤት እየመጡ መንፈሳዊ ትምህርት እንዲማሩ ያደርጉ ዘንድ ወላጆችን አደራ በማለት በቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ የአቀባበሉ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።

ከዚያ ቀደም ሲል ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ንግግር አድርገዋል ። ባደረጉትም ንግግር የዛሬው በአል የተደራረበ ነው አንደኛ አረጋዊው ስምዖን ክብሉት የታደሰበት ዕለት ሲሆን ሁለተኛ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዚህ ሀ/ስብከት ተገኝተው ለሕዝበ ክርስቲያኑ ቡራኬ የሰጡበት በመሆኑ ነው ፤ አባትንም ከማየት የበለጠ ደስታ የለምና ሁላችሁም ተደስታችኋል ፤ ብለዋል ፤ ብፁዕነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል ቅዱስነታቸው እንደ ሐዋሪያው ጳውሎስ ያለ ገድል አላቸው ሐዋሪያው ጳውሎስ ከሐዋርያት አብልጦ እንዳስተማረ ቅዱስነታቸውም ከቀደሙ አባቶቻችን ይልቅ በበለጠ በየአህጉረ ስብከቱ እየዞሩ ያዘኑትን ያጽናናሉ የተቸገሩትንም ይረዳሉ ፤ የደከሙትን ያበረታታሉ፤ ያልተማሩትን ያስተምራሉ ፤ በማለት ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ቀጥሎም የሀ/ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አለቃ መኮንን ገ/መድኀን ስለሀገረ ስበከቱ የሥራ እንቅስቃሴ በሰፊው ገልጸው ሲያበቁ ከንግግራቸው በማያያዝ ቅኔዎችን አበርክተዋል ። ከሊቃውንቱም መካከል የተፈቀደላቸው ምሁራን በየተራ ወደ ቅዱስነታቸው እየቀረቡ ቅኔ ሰጥተዋል ። በዚሁ ዕለት በ፰ ሰዓት ስለቅዱስነታቸው ክብር በመንበረ ጵጵስናው የምሳ ግብዣ ተደርጓል ፤ በግብዣውም ላይ ጥሪ የተደረገላቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖች የአራቱም አውራጃዎች ሊቃነ ካህናትና ምክትሎቻቸው የሰበካ ጉባኤ አባላት የሁለቱ አድባራት ካህናት የሰንበት ት/ቤት ተማሮች በርከት ያሉ ምእመናት ተገኝተዋል ።

በ፲፩ ሰዓት ላይ አዲስ ሊሠራ የታቀደውን የሲቀላ ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የመሠረት ደንጊያ ለማስቀመጥ ቅዱስነታቸው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው ከቦታው በደረሱ ጊዜ ካህናቱ የሰንበት ተማሪዎች በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ምእመናን በልልታና በጭብጨባ ተቀብለዋቸዋል ። ፫ ሕፃናትም ዕቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ። ቅዱስ ፓትርያርኩ ግራና ቀኝ የተሰለፉትን ምእመናን በመስቀላቸው እየባረኩ ወደ ቤተ መቅደሱ በመግባት ጸሎት አድርገው በተዘጋጀላቸው ስፍራ እንደቆሙ ጸሎተ ወንጌል ተጀምሮ

እስመ ሠምሩ አግብርቲከ ዕበኒሃ ወአክበርዎ ለመሬታ


ወይፈርሁ ስመከ አሕዛብ ፤ የሚለው መዝሙረ ዳዊት ተሰብኳል ፤ ወደ አማርኛ ሲተረጐም አገልጋዮችህ ደንጊያዋን ወደዋልና መሬቷን አከበሩ አሕዛብም ስምህን ይፈራሉ ማለት ነው ቅዱስነታቸውም ማቴ ፲፯, ፲፫—፳ አንብበውኪዳን ከደረሰ በኋላ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የመሠረቱን ደንጊያ እንዲያኖሩላቸው ቅዱስነታቸውን ጠይቀዋል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመሠረቱን ደንጊያ አኑረው በዓራቱም ማዕዘን እየተዘዋወሩ ባርከው ሲያበቁ በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር እንደተቀመጡ ፤ የሰንበት ት/ቤት ተማሮች "አማን በአማን ተክለ ሃይማኖት ፀሐይ" የሚለውን ያሬዳዊ መዝሙር ዘምረዋል በተጨማሪም "አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሊቀ ጳጳሳት በምእመናን ተመርጠህ የተሾምክ የአምላክንም ትእዛዝ በጽድቅ የፈጸምክ" የሚል መዝሙር ዘምረዋል ። ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ሊቀ ጳጳስ የመንፈሳዊ ፍርድ ቤት ሐላፊ ንግግር አድርገዋል ። ብፁዕነታቸው ባደረጉ-





ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የቤተ ክርስቲያኑን የመሠረተ ድንጋይ ሲያኖሩ





ቅዱስነታቸው ደብረ ቅ. ጊዮርጊስ ሲደርሱ የተደረገላቸውን አቀባበል ይህንን ይመስል ነበር

ትም ንግግር "እግዚአብሔር ወጣኔ ኩሉ ወፈጻሜ ኩሉ" ሥራውን የሚጀምርና የሚፈጽም እግዚአብሔር ነው" በሚል ርእስ ተንሥተው ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል ፤ በሰጡትም ፤ ማብራሪያ በዚህ ቤተ ክርስቲያን መቃኞ የተሠራው በ፲፱፻፳፭ ዓ.ም መሆኑን ገልጸው ቤተ ክርስቲያኑ ባለፉት ዓመታት ዕድገት አሳይቶ በ፲፱ ዓመቱ አሁን በቅዱስ ፓትርያርኩ መሠረት ማስጣሉ እጅግ የሚያስደስት ነው ብለዋል ። ብፁዕነታቸው ማብራሪያቸውን በመቀጠል ፤ ቅድስነታቸው በወላይታ ሳሉ የሠሯቸውን የሚያስመሰግኑ ተግባሮች አስታውሰው ዛሬ በዚህ ሀገረ ስብከት ቤተ ክርስቲያንን በከፍተኛ ደረጃ እያገለገሉ የሚገኙት ሊቃውንትም ቀደም ሲል በቅዱስነታቸው የተሰባሰቡ ናቸው ብለዋል ።

በተጨማሪም ይኸው ሀ/ስብከት ቀደም ሲል በቅዱስ ፓትርያርኩ መልካም ሥራ የተደሰተ መሆኑን ገልጸው ፤ ከሐዲሳን ሊቃነ ጳጳሳት ደግሞ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ወደዚሁ ሀ/ስብከት በመላካቸው ከፍተኛ የሥራ ፍሬ የታየ መሆኑን በመግለጽ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጸሎተ ቡራኬ ሲያደርጉ ለቤተ ክርስቲያን ሁለት ስሞች አሏት አንደኛው ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ሁለተኛው ቤተ እግዚአብሔር ነው ይኸውም የክርስቲያኖችና የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው በሌላም በኩል ቤተ ክርስቲያን የምትመሰለው በጽርሐ አርያም ነው ከቤተ ክርስቲያን ለጸሎት ለስግደት ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚገኝ ሁሉ በደብረ ጽዮን በጽርሐ አርያም ይገኛል ካሉ በኋላ ቅዱስነታቸው መንፈሳዊ መልእክታቸውን በመቀጠል ።

ቤተ ክርስቲያን ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙባት የክርስቲያኖች ሁሉ ቤት ናት ይህችን የጋራ ቤታችሁን ቤተ ክርስቲያን ተባብራችሁ እንድትሠሩ አደራ እንላችኋላን አሁን ከዚህ ቦታ ላልተገኙትም ክርስቲያኖች ንገሯቸው ሁላችሁም ተባብራችሁ ቤተ ክርስቲያኑን ሠርታችሁ ፤ በቶሎ እንድትፈጽሙ የኦርቶዶክስ እምነታችሁንም እንድታጠናክሩ አሳስባችኋለሁ ብለዋል ።

ቅዱስነታቸው ምክራቸውን በመቀጠል እንደ ሕዝቡ ጠባይ የሚያስተምሩ አባት አቡነ ዘካርያስ ስላሏችሁ እድለኞች ናችሁ የእርሳቸውን መመሪያ አክብራችሁ መሥራት አለባችሁ ፤ በማለት አባታዊ ምክር ከሰጡ በኋላ ከዚያው በመቀጠል ይህ ደብር እስከዛሬ ድረስ ስም ያልተሰጠው በመሆኑ ከዛሬ ጀምሮ ደብረ ኃይል ተብሎ እንዲጠራ ደብሩን የሚያስተዳድረው መልአከ ኃይል እንዲባል በደብሩ የሚያገለግሉ ምሁራን ርእሰ ደብር ፤ ሊቀ ጠበብት ፤ ቀኝ ፤ ጌታ ግራ ጌታ ተብለው ይሾማሉ ሲሉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መመሪያ ሰጥተዋል ይህንን መንፈሳዊ መመሪያ በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ በሰማ ጊዜ ደስታውን በጭብጨባና በልልታ ገልጿል በመጨረሻም ጸሎተ ቡራኬ አድርገው በዚያ የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ። ቅዱስነታቸውም ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር ወደ መንበረ ጵጵስናው ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ.ም ከክብር ተከታዎቻቸው ጋር በመሆን ከጧቱ ፪ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ከዐርባ ምንጭ ተነስተው ወደ ጩንቻ መድኃኔ ዓለም ካህናት ማሠልጠኛ ጉዟቸውን ቀጥለዋል ፴ ኪ.ሜ. ርቆ ከሚገኘው አቸሎ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ሲደርሱ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት በሰበካው የሚኖሩ ምእመናን የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች በመዝሙርና በልልታ ተቀብለዋቸዋል።

ሁለት ሕፃናትም ዕቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ቅዱስነታቸው ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ገብተው ጸሎት ካደረጉ በኋላ በተዘጋጀላቸው ዓውደ ምሕረት ላይ እንደተቀመጡ የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ ሊቀ መንበር መምሬ ዞማ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ሥራ በዝርዝር የሚያስረዳ ሪፖርት አንብበዋል ።

ቀጥሎም ቅዱስ ፓትሪያርኩ ጸሎተ ቡራኬ ሲያደርጉ በአስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ሉቃስ ፲፱ ፴፭ ወገባችሁ የታጠቀ ፤ መብራታችሁም የበራ ይሁን የሚለውን ጠቅሰው ወገብን መታጠቅ ማለት በሃይማኖት መጽናት ሲሆን መብራት የተባለ ደግሞ መልካም ሥራ ነው መጾም መጸለይ ቤተ ክርስቲያንን ማደስና መሥራት የተመሰገኑ ሥነ ምግባራት ናቸው ። መብራት ጨለማን እንደሚያርቅ መልካም ሥራም ሰይጣንን ያርቃል ወደ መንግሥተ ሰማይም ይመራል ፤ ስለዚህ ሃይማኖታችሁን አጽንታችሁ ምግባራችሁን አሳምራችሁ በፍቅርና በሰላም ኑሩ የቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org



ቅዱስነታቸው ለሠለጠኑት የምስክር ወረቀት ሲሰጡ

አምላክ ይጠብቃችሁ ልጆች በዕረፍት ጊዜያቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ እንዲማሩ እንድታደርጉ አደራ እንላችኋላን በዚህ ቤተ ክርስቲያን የጐደለ ቢኖር እንሞላለን በማለት ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ቅዱስነታቸው መንገዳቸውን ቀጥለዋል ።

ዶርዜ ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ሲደርሱ ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀልና ጽንሐሕ ይዘው የሰንበት ተማሮዎች ከበሮ ይዘው እየዘመሩ ምእመናኑ በልልታና በጭብጨባ ተቀብለዋቸዋል ፫ ሕፃናትም አበባ አበርክተውላቸዋል ፡ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ገብተው ጸሎት ካደረጉ በኋላ ወደ ዓውደ ምሕረቱ ወጥተው ቅዱስ ፓትርያርኩ ስለተደረገላቸው አቀባበል አመስግነው የሚከተለውን መንፈሳዊ መልእክት አስተላልፈዋል ፡ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ የሚከተለኝ ሁሉ በብርሃን ይመላለሳል ጨለማ አያገኘውም ብሏል ፤ እንደምታውቁት ጨለማ ሁሉን ያስፈራል ሥራንም ለመሥራት አያስችልም መንገድም በጨለማ ቢሔዱ እንቅፋት ይመታል እሾህም ይወጋል በብርሃን ግን ሁሉን ለመሥራት ይቻላል እንቅፋትም አያነቅፍም እሾህም አይወጋምና ።

በክርስቶስ ያመናችሁ ሁሉ መሰናክል አይገጥማችሁም ብርሃን የተባለ ክርስቶስ ነውና ሁሉንም ነገር ያበራልችኋል እርሱን ብቻ ከልብ ማመን ያስፈልጋችኋል በእርሱ ያመነ ሰው በብርሃን እንደሚመላለስ ሰው ችግር አይገጥመውም ሁላችሁም በክርስቶስ እምናችሁ በመልካም ሥራ ጸንታችሁ ኑሩ በማለት ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ጉዟቸውን ቀጥለዋል ።

ከዚያም በመንገዳቸው ዳር የሚገኘውን የላካና መልዶ ደብረ ገነት ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያንን ጐብኝተዋል በቤተ ክርስቲያኑም ቅጽረ ግቢ እንዳሉ የሰበካ ጉባኤው ሊቀ መንበር ወደ ቅዱስነታቸው ቀርበው ቤተ ክርስቲያኑን ለማሠራት ፕላን ተዘግጅቶ ገንዘብ በመሰብሰብ ላይ መሆኑን አስረድተዋል ፤ ቅዱስነታቸውም የሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ በቶሎ እንዲቋቋም አዝዘው ወደ አዲስ አበባም መጥቶ ኮሚቴው በቅዱስ ሲኖዶስ በኩል ርዳታ ቢጠይቅ የማይነፈገው መሆኑን ተስፋ ሰጥተዋቸዋል ።

ከዚያ በኋላ ቅዱስነታቸው ጉዟቸውን በመቀጠል ጨንቻ መድኃኔ ዓለም ካህናት ማሠልጠኛ ሲደርሱ ካህናት የሰንበት ት/ቤት ተማሮዎች የሰበካ ጉባዔ አባላት በአካባቢው የሚኖሩ ምእመናን በመዝሙር ፤ በልልታና በጭብጨባ ተቀበለዋቸዋል ፤ ሁለት ተማሪዎችም ዕቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ጸሎት ካደረጉ በኋላ ወደ ማሠልጠኛው አምርተው በማሠልጠኛው ትምህርት ቤት ከተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር ላይ እንደተገኙ ጸሎተ ወንጌል ተጀምሮአል ።

እስመ መምህረ ሕግ ተሰብኮ ሲያበቃ ቅዱስነታቸው ከዮሐንስ ወንጌል ፲, ፩—፲፯ የሚገኘውን አንብበው ሲፈጽሙ የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አለቃ መኮንን ገብረ መድኅን ስለ መርሐ ግብሩ ቅደም ተከተል ገለጻ አድርገዋል።

በመጀመሪያ የካህናት ማሠልጠኛው ርእሰ መምህር ስለትምህርት ቤቱ ይዞታ ገለጻ አድርገው ሲያበቁ ሠልጣኞቹ ካህናት በሠረገላ ተመስለት ቤተ ክርስቲያኑ ለተክለ ሃይማኖት አንተ ዓርባዕቱ ገበዋቲሃ ወዓርባዕቱ ወንጌላውያን የሚል ግሥ ገሠው ለ፳ ደቂቃ ሲያሸበሽቡ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎችም

ሐውጾነ በምህረት ሊቀ ጳጳሳት ባሕረ ጥበባት መምህረ ሰላም

ተክለ ሃይማኖት ፤

ቀድስ ሕዝበከ ዲበ ዝንቱ ሀገር ቅድስት ሀገረ ጋሞ ጎፋ

ዘሐደሳ ዘካርያስ የሚል መዝሙር ዘምረዋል ። ቀጥሎም ለ፰ ወራት የሠለጠኑት ፲፯ ካህናት በቅዱስነታቸው እጅ ለዕውቀታቸው መለኪያ የተጋጀውን የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የምስክር ወረቀቱን ከሰጡ በኋላ መንፈሳዊ መመሪያና ምክር ሰጥተዋል በሰጡትም መመሪያ ትምህርትን አውቆ ማሳወቅ ትልቅ ተግባር ነው የማንኛውም መመሪያ ዕውቀት ስለሆነ ተምሮ አውቆ ያላወቁትን አስተምሮ እንዲያውቁ ማድረግ ይገባል ።

በሥጋዊ አስተዳደርም ቢሆን የተማረና ያወቀ ሰው ብዙ ሥራዎችን ለመሥራት ይችላል በሰማይ የሚበሩ በምድር የሚሽከረከሩ ፤ በባሕር ላይ የሚንሳፈፉ መሣሪያዎች የተፈለሰፉት በተማሩ ሰዎች ነው እኛ ስናያቸው የተደከመባቸው አይመስለን ይሆናል ግን ሳይማሩ ሳይደክሙ ዕውቀት ሊገኝ አይችልም ካሉ በኋላ ቅዱስነታቸው ወደ መንፈሳዊ ተግባር መለስ ብለው በመንፈሳዊ



በኩልም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ሲል የሠራውን ሥራ ስለሰው ፍቅርም የተቀበለውን ጸዋትወ መከራ ለማወቅ የሚቻለው በትምህርት ነው ይህ ማሠልጠኛ የዕውቀት መፍለቂያ መሆኑ የታወቀ ነው ፤ በዚህ ቦታ ተምረው ሠልጥነው የሚወጡት ካህናት ባላቸው ዕውቀት ቤተ ክርስቲያንን የማገልገል ግዴታ አለባቸው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ያስተምርበት በነበረው ወቅት ከዕለታት አንድ ቀን አልፎ ሲሄድ አሥር ለምጻሞች ወደ እርሱ ቀርበው አድነን ብለው በለመኑት ጊዜ ፈውሶ ሲያበቃ ሄዳችሁ ራሳችሁን ለካህን አስመርምሩ ብሏቸዋል ይህም የሚገልጸው የካህናትን ክብር ነው ፤ ካህናት ከሠሩበት ክብራቸው እጅግ ከፍ ያለ ነው ትምህርትን ተምሮ ካላስተማሩበት ያስወቅሳል በዚህ መሰልጠኛ ገብታችሁ ለተወሰነ ጊዜ የተማራችሁ ሁሉ ያልተማሩትን ወገኖቻችሁን እንድታስተምሩ አደራ እንላችኋለን ።

ለምሳሌ ገበሬ ዘሩን ዝም ብሎ በጎተራ ቢያስቀምጠው ያው ነው አይጨምርም ቢዘራው ግን ይበዛል ከራሱ አልፎ ለሌላውም ይተርፋል ትምህርትም በዘር ይመሰላል ቢያስተምሩበት ወገንን ይጠቅማል ከእግዚአብሔርም ዋጋን ያስገኛል ባያስተምሩበተ ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ያስወቅሳልና የተማራችሁትን በንቃትና በትጋት እንድታስተምሩ አደራ በማለት ቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ አድርገዋል ።

ከዚያ ቀደም ሲል ብፁዕ አቡነ ገሪማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሱዳን ሊቀ ጳጳስ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተጠ/ዋና ጸሐፊ ትምህርት ሰጥተዋል ። በሰጡትም ትምህርት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ፫ ዓመት አስተምሮ አሠልጥኖ የሰጣቸው መመሪያ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችሁ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" በማለት ምሥጢረ ጥምቀትን እንዲያስተምሩ ነበር የላካቸው ካሉ በኋላ ብፁዕነታቸው ትምህርታቸውን በመቀጠል ሐዋርያት ከክርስቶስ ጋር ሳሉ ጥያቄን ያቀርብላቸው እንደነበር ገልጸው ያም ጥያቄ የሚደርስባቸውን ልዩ ልዩ ፈተና ለመውጣት የሚችሉ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነበር ብለዋል ትምህርታቸውን በመቀጠል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው የደረሰባትን መውደቅና መነሣት በዝርዝር ገልጸው በአሁኑ ጊዜ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መዋዕለ ሢመት የምታደርገውን ትምህርታዊ እንቅስቃሴ በማድነቅ ለዚህ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ካህናቱም ሆኑ ምእመናኑ መተባበር ያለባቸው መሆኑን አሳስበው ብፁዕ አቡነ ገሪማ ትምህርታቸውን ፈጽመዋል ።

ቀጥሎም በማሠልጠኛው አዳራሽ የምሳ ግብዣ ተደርጓል ። ከግብዣው በኋላ ቅዱስነታቸው በሠልጣኞች ካህናት የሚሠሩትን የቀርቅሃ ወንበሮችና ጠረጴዛዎችን ፤ የፍራፍሬ ማቅረቢያዎችን ፤ የቁምና የልብስ ማስቀመጫ ሳጥኖችን መስቀሎችን አካላቸው ሽባ ለሆነ የሚያገለግሉ የእንጨትና የብረት ምርኩዞችን ጫማዎችን አንድ በአንድ እየተዘዋወሩ ከተመለከቱ በኋላ በዚያ የሚሠለጥኑ ፤ ካህናት ጠንክረው ተምረው ከተመረቁ በኋላ በተመደቡበት ቦታ ራሳቸው አቋቁመው እንዲሠሩ መመሪያ ሰጥተዋል ከዚያም በኋላ ቅዱስነታቸው ከክብር ተከታዎቻቸው ጋር ወደ አርባ ምንጭ ተመልሰዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የካቲት ፲ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም መንፈሳዊ ጉብኝታቸውን በመቀጠል ፱ ሰዓት ተኩል ሲሆን የክብር ተከታዎቻቸውን አስከትለው ጉዟቸውን ወደ ጫሞ ሐይቅ ቀጥለው በሦስት ሰዓት ከሐይቁ ዳርቻ ደርሰዋል ቅዱስነታቸው የሐይቁን አካባቢ እየተዘዋወሩ ለጥቂት ደቂቃ ከተመለከቱ በኋላ ለጉብኝት በተዘጋጀው መርከብ ላይ በመሳፈር የባሕር ላይ ጉዞ አድርገዋል ፤ በጉዟቸውም አዞ መሰብሰቢያ (አዞ ገበያ) እየተባለ የሚጠራውን ተመለከተዋል በዚያም ቦታ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የአዞ መንጋዎች ሲርመሰመሱ ይታያሉ ብዙዎቹ በባሕሩ ዳር ጉቶ መስለው ተጋድመው ይታያሉ አንዳንዱ አፋቸውን ዋሻ አስመስለው ከፍተው ተኝተዋል ከአጠገባቸው ጉራማይሌ መልክ ያላቸው አሞሮች ሰልፈኛ መስለው ቆመው የታያሉ ግን አዞዎችና አሞራዎቻ አይጣሉም በመካከላቸው የስምምነት ውል የተፈራረሙ ይመስላሉ ።

በዚህ ሐይቅ ጉማሬዎች በብዛት ስለሚገኙ ብቅ ጥልቅ እያሉ ባሕሩን ሲከፋፍሉት ዕውብ ድንቅ ያሰኛል ዓሣዎቻም ከባሕሩ ብቅ በማለት እንደጦር ሲወረወሩ ይታያሉ ፤ በዚህ አኳኋን ቅዱስነታቸው በባሕር ላይ አንድ ሰዓት ተኩል ጉዞ ካደረጉ በኋላ ወደ ወደቡ ወጥተው ዓርባ ምንጭ ተብሎ ወደሚጠራው ቦታ አምርተዋል ፤ ከቦታው ደርሰው በአስጎብኝዎች አማካይነት እየተዘዋወሩ ዉሃው ምንጮች የሚፈልቁባቸውን አንድ በአንድ በመመልከት ለጉብኝቱ መታሰቢያ የሚሆን ፎቶ ተነሥተዋል ።

በዚያም ለሚሠሩ ወዝአደሮች የገንዘብ ችሮታ አድርገውላቸዋል ከዚያም በኋላ ከክብር ተከታዎቻቸው ጋር ወደ መንበረ ጵጵስናው ተመልሰዋል ፤ በዚያም የመሰነባበቻ ግብዣ ከተደረገ በኋላ በመንፈሳዊ አገልግሎት ሲደክሙ ለሰነበቱት ምእመናንና ምእመናት የዕፀ መስቀል ስጦታ አድርገውላቸዋል ቀጥሎም ቅዱስነታቸው በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ግጽረ ግቢ የተቋቋሙትን የልማት ሥራዎች ጎብኝተዋል የተቋቋሙትም የልማት ሥራዎች ሹራብ ፤ ጋቢ ፤ ኩታ ፤ የአልጋ ልብስ ወዘተ ይሰራባቸዋል በተጨማሪም በመሠራት ላይ የሚገኘውን የስብከተ ወንጌል አዳ



www.ethiopianorthodox.org

# ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ

የቅዱስ ጊዮርጊስ አባቱ አንስጣስዮስ ሲሆን እናቱ ቴዎብስታ ትባላለች የአባቱ ሀገር ቀጳዶቅያ የእናቱ ሀገር ልዳ ነው ።

አባቱ በዚያን ጊዜ ንጉሥ የነበረው የዱድያኖስ ሹም ነበር የቅዱስ ጊዮርጊስ እድሜው ሃያ ዓመት ሲሆን ወላጅ አባቱ ሞተበት በአባቱ ሞት ሐዝና ለጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ የአባቱን ሹመት ለመጠየቅ ወደ ዱድያኖስ ሄደ ከዚያም በደረሰ ጊዜ ዱድያኖስ ጣዖት አቆሞ ራሱም ከመስገዱ ሌላ ሕዝቡንም ሲያሰግድ አገኘው የዱድያኖስን አምልኮ ጣዖት ለመቃወም እንዲችል ወደ ቤቱ ተመለሰና የነበረውን ሀብት ሁሉ ለችግረኞች አከፋፍሎ ሰጠ ። ከዚያም በኋላ ወደ ዱድያኖስ ተመልሶ ሂዶ በአደባባይ ቆመና የሚሰግድለት ጣዖት የማያድን ከንቱ መሆኑንና የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት አስተማረ ።

ንጉሡ ዱድያኖስ የቀዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ሕዝብን የሚማርክና የሚያስጋ ሆኖ ስላገኘው እርሱ ላቆመው ጣዖት ቢሰግድ ሹሞ ሸልሞ በክብር እንደሚያስቀምጠው መላልሶ ነገረው ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን የዱድያኖስን ሀሳብ አልተቀበለውም የሚያድንና የሚገድል ሰማይንና ምድርን የፈጠረ አምላክ ብቻ ስለሆነ ለጣዖት መስገዱን ትታችሁ በአንድ አምላክ እመኑ እያለ በማስተማሩ በዙ ሰዎች ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ተመልሰዋል ።

ዱድያኖስ ቅዱስ ጊዮርጊስን ለመግደል ስለፈለገ አንድ አትናስትያ የሚባል ጠንቋይና አስማተኛ ሰው አስመጥቶ የሚገድል መርዝ ቀምሞ እንዲጠጣው አደረገ ቅዱስ ጊዮረጊስ መርዙን ከአስማተኛው እጅ ተቀብሎ ቢጠጣውም ምንም ጉዳት ሊደርስበት አልቻለም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌሉ "በስሜ ላመኑት ብዙ ተአምራት ይደረግላቸዋል ። የሚገድል መርዝ ቢጠጡ አይገላቸውም ብሎ ተናግሯልና ማርቆስ ፲፮.፲፰ ።

በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በጣም ተደነቁ የሚገድለውን መርዝ አዘጋጅቶ ለቅዱስ ጊዮርጊስ የሰጠውም አስማተኛ ጠንቋይ የጥንቁልና ሥራውን ርግፍ አድርጎ ,ትቶ በክርስቶስ ስም አምኖ በመጠመቅ በሰማዕትነት ሞቷል ።

ዱድያኖስ በቅዱስ ጊዮርጊስ ላይ እንዲፈጸመበት ያሰበው ክፉ ሥራ ሁሉ ሳይሳካለት በመቅረቱ በጣም ተናደደና የብረት መጋዝ አሠርቶ በዚያ እየተገዘገዘ እንዲገደል ስላዘዘ በመጋዝ ተገዝግዞ ከሞተ በኋላ ክርስቶስ ወዲያውኑ አሥነሥቶታል ። ተነሥቶም ዝም ብሎ አልተቀመጠም ወዲያውኑ ማስተማሩን ቀጥሏል ። በትምህርቱም ከ፫ሺህ የበለጡ ሰዎችን አሳምኖና አጥምቆ በሰማዕትነት እንዲሞቱ አድርጓል ሰማዕቱ ሳይፈራ በድፍረት ፸ ነገሥታት በሚገኙበት አደባባይ ሲያስተምር የተቀመጡባቸውን ወንበሮች አለምልሞ እንዲያሳያቸው ጠየቁት ቅዱስ ጊዮርጊስም ወደ ፈጣሪው በመጸለይ ነገሥታቱ ተቀመጠውባቸው የነበሩትን ወንበሮች አለምልሟቸዋል ።

ይሁን እንጂ ሰባው ነገሥታት ከክፉ ሥራቸው አልታገሡም እሳቱን ግር አድርገው አሰነድደው ብረት ምጣድ በመጣድ በዚያ ላይ ሰውነቱን አሳርረው በመፍጨት ደበረ ይድራስ ከተባለ ተራራ ላይአውጥተው በነፋስ አዝርተውታል ። ነገር ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሁንም ከሞት ስላስነሳው እንደገና ማስተማሩን ቀጥሏል ።

ነገሥታቱ በሁኔታው ስለተደነቁ የሞተ ሰው አስነሥተህ ብታሣየን በአንተ አምላክ እናምናለን አሉት ቅዱስ ጊዮርጊስም ወደ ፈጣሪው በመጸለይ ከወንዶችና ከሴቶች ወገን ብዙ ሙታንን ከማስነሳቱም ሌላ ያላመኑትም በክርስቶስ ስም እንዲያምኑ አድርጓቸዋል ።

ሰማዕቱ ይህንን ሁሉ ተአምራት ሲያደርግ የተመለከቱ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ አምነው ተጠምቀው ራሳቸው ስለ ክርስቶስ አዳኝነት እየመሰከሩ በሰማዕትነት ሲሞቱ አንዳንድ ሰዎች ግን ቅዱስ ጊዮርጊስ የፈፀመውን ገቢረ ተአምር ምትሐት ነው እንጂ እሙን አይደለም በማለት በክርስቶስ እንዳያምኑ ሰዎቹን ይከለክሉ ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን ቅዱስ ጊዮርጊስን ወስደው ከአንዲት ደሃ ሴት ቤት ውስጥ ከምሰሶው ከወጋግራው ጋር አሠሩትና ወደ ፈጣሪው ቢጸልይ የታሠረበት ወጋግራ ለመለመና ቅጠል አውጥቶ ትልቅ ዛፍ ሆነ ከዚያም እንዳለ አንድ ዲዳ ደንቆሮና ዕውር ልጅ አመጡና እንዲፈውስላቸው ጠየቁት እርሱም ወደ ፈጣሪው በመጸለይ እንዲናገር እንዲሰማና እንዲያይ አድርጎላቸዋል ።

ንጉሡ ዱድያኖስ ይህንን ዜና በሰማ ጊዜ በጣም ተናደደ ጊዮርጊስን ከታሠረበት አውጥተው እንዲገርፉት አሽከሮቹን አዘዛቸው ። እነርሱም ሰማዕቱን ከእሥር ቤት አውጥተው ከገረፉት በኋላ ወደ አውድማ አስገብተው እንደ እህል በበሬ እግር እንዲጠቀጠቅ በዱላ እንዲወቃ አድርገውታል ። ነገር ግን ኃይለ እግዚአብሔር ስላልተለየው እንደገና ተነሥቶ ማስተማሩን ቀጠለ ።

ዱድያኖስ የሚያደርገው መላ ቅጡ ስለጠፋው ሴት ልጁን አግብቶ እንደራሴ እንዲሆን ጠየቀው ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ የክርስቶስን ቃል በዱድያኖስ ቤተ ሰብእ ውስጠ ለማስተማር መልካም አጋጣሚ ሆኖ ስላገኘው ነገሩን የተቀበለ መስሎ ገባና ማስተማሩን ቀጠለ ከትምህርቱም ጣዕም የተነሣ የዱድያኖስ ሚስት በክርስቶስ ስም አምና ተጠመቀች ዱድያኖስ ተናዶ በሰይፍ ስላስቆረጣት የሰማዕታትነትን የክብረ አክሊል ለመቀዳጀት በቅታለች ።

ከዚህ በኋላ የንጉሡ ዱድያኖስ የቅርብ አማካሪ የሆኑ ሰዎች ቅዱስ ጊዮርጊስ በሰይፍ አንገቱን እንዲቆረጥ ወስነው አቀረቡለት ። ቅዱስ ጊዮርጊስ ይህንን ዜና በሰማ ጊዜ በጣም ተደሰተ ወደ ፈጣሪውም በጸለየ ጊዜ እሳት ከሰማይ ወረዶ ሰባውን ነገሥታት ከእነሠራዊታቸው አቃጠላቸው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለቅዱስ ጊዮርጊስ ተገልጦ ሰምህን ጠርቶ የጸለየ በስምህ ቤተ ክርስቲያን ያሠራ መታሰቢያህንም ያደረገውን በስምህ የተራቡትን ያበላውን የተጠሙትንም ያጠጣውን ሰው ሁሉ እምርልሃለሁ ። የሠራውንም ኃጢአት እደመስስለታለሁ በባሕርና በየብስ ሲጓዙ ችግር ደርሶባቸው በጸና ተይዘው ሥቃይ ጸንቶባቸው ያንተን ሥም ጠርተው ቢለምኑኝ ከደረሰባቸው ችግር ሁሉ ፈጥኜ አድናቸዋለሁ ብሎ ቃል ኪዳንን ከሰጠው በኋላ ወደ ሰማይ አርጓል ።

ከዚያ በኋላ ቅዱስ ጊዮርጊስ በሰይፍ አንገቱን ተቆርጧል ። በተቆረጠም ጊዜ ከአንገቱ ደም ውሀ ወተት ወጥቷል። ለታግደሎው ዋጋ የሆኑ ሰባት አክሊላተ ክብርም ወረደውለታል ምእመናንም ሥጋውን ወስደው ልዳ በምትባል ሀገር ቤተ ክርስቲያን ሠርተው በክብር አስቀምጠውታል ። በክርስቶስ ስም አምነን የተጠመቅንና በሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቃል ኪዳን የምንማፀን ክርስቲያኖች ሁሉ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም በታነፁ አብያተ ክርስቲያናት በመገኘት መጸለይ በሰሙ የተራቡትን ማበላት የተጠሙትን ማጠጣት ይገባል ጻድቁን በጻድቅ ስም የተቀበለ የጻድቁን ዋጋ ያገኛል ተብሎ ተጽፎአልና ።

ቀ.ልሣነወርቅ በዛብሀ

ራሽ የሀ/ስብከቱን ጽ/ቤት ጎብኝተዋል። እንዲሁም በሀ/ስብከቱ ለሚያገለግሉ ካህናትና ለሰንበት ት/ቤት ማስፋፊያ የሚሆን ብር ፲ሺህ ለክፍለ ሀ/ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዘካርያስ ሰጥተዋል ።

ዕለቱ ወደ አዲስ አበባ የሚመለሱበት በመሆኑ ፱ ሰዓት ከ፴ ሲሆን ቅዱስነታቸው ከክብር ተከታዎቻቸው ጋር በመሆን ወደ ዓርባ ምንጭ የአየር ማረፊያ ጉዟቸውን ቀጥለዋል ፤ በዚያም ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የክፍለ ሀ/ምክትል አስተዳዳሪ ጓድ ደምጸ ገብረ መድኅን የሀ/ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አለቃ መኮንን የሰንበት ተማሮች ካህናት የሰበካ ጉባኤ አባላት በርከት ያሉ ምእመናን በአየር ማረፊያው በመገኘት ሸኝተዋቸዋል ።

ቅዱስነታቸው ከተከታዎቻቸው ጋር ከዓርባ ምንጭ ተነሥተው በአየር ፩ ሰዓት ከ፲፮ ደቂቃ ከበረሩ በኋላ ቦሌ አየር ማረፊያ ሲደርሱ የመንበረ ፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ ሊቀ ሥልጣናት ኤልያስ አበበ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘርይሁን የውጭ ሀገር አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ ሊቀ ካህናት ቅፍሌ ገብረ መስቀል ።

.እንኳን ደህና መጡ በማለት ተቀብለዋቸዋል ፤ ቅዱስነታቸው በጋሞ ጎፋ ሀ/ስብከት ያደረጉት መንፈሳዊ ጉብኝት በዚህ ይጠቃለላል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ደከመኝ ልረፍ ሰለቸኝ ልቀመጥ የማይሉ ታላቅ መንፈሳዊ አባት በመሆናቸው በኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት እየተዘዋወሩ በመኅብኘት የሚሰጡት አባታዊ ቡራኬ የሚያስተላልፉት መንፈሳዊ መልእክት ካህናትንም ሆነ ምእመናንን ለመልካም ሥራ የሚያነቃቃና የሚቀሰቅስ ነው ።

ቅዱስነታቸው ከሚሰጡት መመሪያና ከሚያስተላልፉት አባታዊ መልእክት የተነሣ በመዋዕለ ሢመታቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ታንፀዋል የፈረሱትም ታድሰዋል የካህናትም ኑሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመሔድ ላይ ይገኛል ወደ ፊት ከአሁኑ በበለጠ ያልታነፁት አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ ያረጁት እንዲታደሱ የካህናትም ኑሮ ከአሁኑ በበለጠ እንዲሻሻል ለቅዱስነታቸው ሰፊ ዘመናትን ረዥም ወራትን እንመኛለን ።

የዜናው አቅራቢ
ቀ/ልሣነ ወርቅ በዛብኅ





www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## የመሪጌታ ኑርልኝ የእኔ ሁኖ የሕይወት ታሪክ ባጭሩ

መሪጌታ ኑርልኝ የእኔ ሁኖ በጎንደር ሀ/ስብከት ደብረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ በር ቅዱስ ጊዮርጊስ ከሚባለው ደብር ከአባታቸው አቶ የእኔ ሁኖ ገብርዬ ከእናታቸው ወ/ሮ አሥማረች ወልዱ በ፲፰፻፺፫ ዐ/ም ተመለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርሱ ቄስ አቡነ አረጋዊ ከነበሩት ስመ ጥር መምህር መሪጌታ ወርቄ ገብረ መድኅን ትምህርት ጀምረው ንባብ ፣ ዳዊት ፣ ፀዋትወ ዜማ ተምረዋል ።

ከዚያም ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ ጎና ቅዱስ ገብርኤል ሄደው በዚሁ ደብር ከነበሩት መሪጌታ አፈወርቅ ዘንድ ለ፬ ዓመታት ቅኔ በመማር ለማስተማር ከሚያስችል የዕውቀት ደረጃ ደርሰዋል ።

መሪጌታ ኑርልኝ ለመንፈሳዊ ትምህርት ከፍተኛ ስሜት ስለነበራቸው ጥርጥሪያት ቅዱስ ሚካኤል ወደተባለው ደብር ሄደው በዚያ ወንበር ተክለው ያስተምሩ ከነበሩት መሪጌታ ቢወጣ ዝማሬና መዋሥዕት ለሦስት ዓመታት ከተማሩ በኋላ ወደ እንዳ ቤት በመሄድ ቤተ ማርያም ከተባለችው ደብር ከመሪጌታ ቢተውል ፭ ዓመታት አቋቋም ተምረው መሪጌታ የሚባለውን ሥያሜ አግኝተው አቋቋም በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አሠልጥነው ለቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል።

መሪጌታ ኑርልኝ የእኔ ሁኖ በጣም ተደናቂ ድምፅ ስለነበራቸው በትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት የትምህርት ጓደኞቻቸው ሁሉ የእርሳቸውን ወዝና ለዛ ለማጥናት ብጣም ይጥሩ ነበር በክብረ በዓልም ቀን እርሷቸው እያሉ ማንም ወረብ አይወርብም ነበር ፣ በሚወርቡበትም ጊዜ እርሳቸውን ለማየት ሕዝቡ ይሽቀዳደም እንደነበር በዘመናቸው የነበሩ አዛውንቶች ይናገራሉ ፣

መሪጌታ ኑርልኝ የእኔ ሁኖ ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ የዲቁና ሢመትን ተቀብለዋል ፣ ከተለያዩ መምህራን የገበዩትን መንፈሳዊ ዕውቀት በተለያዩ ቦታዎች ካስተማሩ በኋላ ዙገራ ቅዱስ ገብርኤል ደብር ተቀምጠው እንዲያስተምሩ የአጥቢያው ሕዝብ ስለጠየቋቸውና ቦታውም ለተማሪ አመች በመሆኑ በተጠቀሰው ደብር ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው በማስተማር ተግባር ከቆዩ በኋላ "ብዝሁ ወተባዝሁ ወምልህዋ ለምድር" ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ተብሎ በተነገረው እምላካዊ ቃል መሠረት በተክሊልና በቁርባን ወ/ሮ አሥማረች ጣውነህን አግብተው ፬ ወንዶች ፭ ሴቶች በድምሩ ፱ ልጆችን ወልደዋል ወንዶች ልጆቻቸውንም በሚገባ አስተምረው ለቅስናና ለመምህርነት አብቅተዋቸዋል ።

መሪጌታ ኑርልኝ የእኔ ሁኖ ሙሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ለመሆን ፍላጐት ስለነበራቸው በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. የጎንደር ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት አቡነ ሚካኤል ዘንድ የቅስና መዓርግን ተቀብለዋል ።

ስለዚህ ማኅሌት በሚቆሙበት ጊዜ ቄስ ጥሩልኝ አቡነ ዘበሰማያት ብሎ ይጀምርልኝ አይሉም ነበር ። እራሳቸው መሪጌታና ቄስ ስለነበሩ ሁሉንም አገልግሎት ራሳቸው የሚያከናውኑ በሁሉም ወገን የተሟላ ሙያ ያላቸው ሊቅ ነበሩ።

ከዚህ ሌላ የጣሊያን ፋሽስት ሀገራችን ኢትዮጵያን በግፍ በወረረበት አምስት ዓመታት ከዓርበኞች ጋር በመሆን ከፍተኛ የሆነ ጀብዱ ፈጽመዋል ። ከጣሊያን ጋር ለሚዋጉት ዓርበኞችም ስንቅ ከማቀበላቸውም ሌላ ጀግናውን በማደፋፈር በጦር ሜዳ የወደቀውን በመቅበር ለሀገራቸው የሠሩት ሥራ ምንም የማይረሳ ታላቅ ቁም ነገር ነው።

የመከራው ዘመን አልፎ ሀገራችን ነፃነቷን በተቀዳጀች ጊዜ መሪጌታ ኑርልኝ በደብረ ታቦር አውራጃ በፋርጣ ወረዳ ግራሪያ በተባለው ቦታ ላይ ከጠላት ጋር በተደረገው ጦርነት የፈጸሙትን ጀብዱ በማስታወስ ፊታውራሪ ይማም ተሰማ ለመሪጌታ ኑርልኝ በዘመኑ ከባድ መሣሪያ ተብሎ ይጠራ የነበረውን እንባር ወጨፎ ሸልመዋቸዋል ፣ ጠላት ተሸንፎ እንደሄደ ያበረከቱት ቅኔ

### መወድስ

ተንሥኢ ጽዮን ምድረ ኢትዮጵያ ፣
ወልበሲ ፀምረ ኃይለኪ ዘወረደ ፣ ለቤዛ
ብዙኃን ሕዝብ እስመ ዳግመ ተወልደ ፣
መፀላዕትኪ ይትኀፈሩ ሙኢዮሙ ለጸላ
ዕትኪ ዘበዝኀ ፈድፋደ ፣ ጥበብ በወርኃ
ንግሥ ፣ እስመ ለካህናት አቀመ እንተ
፯ቱ አእማደ

### ለዓለም

እንጉድጉደሂ ዘበላዕሉ ወዘበታ ሀቱ
አርአድ
እንበለ እሳት ዘአንደደ ወዘእንበለማይ
ዘአብረደ
ደጃዝማች አዩ ጳውሎስ በሕገ ዚአሁ
ተፀምደ
አምጣና ሐነፀት ኢትዮጵያ ውስተ ልበ•
አብዳን ማዕፈደ

### ትርጓሜ

ጽዮን የኢትዮጵያ ምድር ሆይ ተነሥ
ተሽ ኃይልሽን ልበሺ ሕዝብን የሚያ
ድን ነፃነት ሁለተኛ ተወልዷልና ጠላቶ
ችሽም ይፈሩ የሚበዙ ጠላቶችሽ ድል

ተመተዋል ። በኢትዮጵያ መንግሥት
ጥበብ ለካህናት ሰባት አምዶችን አቁማ
ለችና ፣

### ለዓለም ትርጓሜ

በላይ እንጉደጉደ በበታችም እንቀጠቀጠ ያለ እሳት አነደደ ያለውሀም አበረደ በሕጉ የተጠመደ ደጃዝማች አዩ ጳውሎስ ፣ ኢትዮጵያ በሰነፎች ልብ ጥበብ አዳራሽን ሠርታለችና ማለት ነው መሪ ጌታ ኑርልኝ በዚህና በሌሎች ቅኔዎቻቸው ስናር በቅሎ ከነሙሉ ጌጧ ረጅም ምንሽር ሙሉ ልብስ ከደጃዝማች አዩ የደብረ ታቦር አውራጃ አስተዳዳሪ ከነበሩት ተሸልመዋል ።

መሪጌታ ኑርልኝ የእኔ ሆኖ ቤተ ክርስትያንን በቅንነትና በታማኝነት ሲያገለግሉ ከኖሩ በኋላ በደረሰባቸው ድንገተኛ ሕማም ምክንያት በተወለዱ በ55 ዓመታቸው በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም.በሞት ተለይተው ወዳጅ ዘመድ ብዙ ሊቃውንት በተገኙበት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት በዙገራ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስትያን ተፈጽሟል ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሀገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት ሲያገለግሉ የኖሩትን አትዘነጋቸውም ስማቸውን በታሪክ መዝገብ አስፍራ ለተከታይ ትውልድ ታስተላልፋለች እንደነ መሪ ጌታ ኑርልኝ የእኔ ሁኖ የታሪክ ባለቤት ሁኖ ለመገኘት ቤተ ክርስቲያንን በቅንነትና በትጋት ማገልገል ያስፈልጋል ።

መሐሪ ጥበቡ ከቅዱስ ጳውሎስ ከ/መ/ት/ቤት



# የብርብር ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ

በጥንታዊነቷ የታወቀችው የብርብር ማርያም ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው በጋሞጐፋ ክፍለ ሀገር በጋሞ አውራጃ በጨንቻ ወረዳ ነው ።

ይህች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ብሉይ በኦሪት ሥርዓትና ደንብ መሠረት የመጻሕፍተ ብሉያት ታሪክና ጸሎት ሥርዓተ መሥዋዕት እምልኮተ እግዚአብሔር እየተፈጸመባት ፳፻ ዘመን ከቆየች በኋላ በዘመነ ሐዲስ ደግሞ በ፭ኛው መቶ እጋማሽ ላይ በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረው አፄ ገብረ መስቀል የዚህችን ጥንታዊት ቤተ መቅደስ ታሪክና ዝና ሰምቶ በኦሪት ሥርዓትና በምኩራብ አይሁድ ደንብ በነበሩት በአክሱም ጽዮን በተድባብ ማርያም በመረጡለ ማርያም በጣና ቂርቆስ ቤተ መቅደሶች ዘመነ ሐዲስን የሚመለከት አዳዲስ ታቦታት ገብተውባቸው ውዳሴና ቅዳሴ ጸሎትና መሥዋዕት እንደሚፈጸምባቸው ሁሉ ፣ በዚህች ብርብር በተባለችው ቤተ መቅደስ ሥርዓተ ሐዲስ ዘመንን የሚመለከት ታቦት ገብቶ ሊወደስባትና ሊቀደስባት ይገባል ብሎ በታቦተ ማርያም ስም ቅዱስ ያሬድ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ አዞ ቅዱስ ያሬድንና አቡነ አረጋዊን አስይዞ በብዙ ድካምና ጉዞ ከአክሱም ጽዮን ተነሥተው ጋሞጐፋ ክፍለ ሀገር ደርሰው ዛሬ ፭ ምንጭ እየተባለ ከሚጠራው ቦታ ላይ አዳር አደረጉ በዚያ አካባቢ የውሃ ምንጭ በፍጹም የለም ነበር ይባላል በዚያች ሌሊት ግን በተአምር ከ ፭ ቦታ ላይ ምንጭ መነጨ ንጉሡ ዓፄ ገብረ መስቀልና ቅዱስ ያሬድ አቡነ አረጋዊ እንደዚህ ያለ አስደሳች ምንጭ ስለፈለቀላቸው እግዚአብሔርን አመሰገኑ በጣምም ደስ አላቸው የአካባቢው ኗሪ ሕዝብም በጣም ተደነቁ ፣

ምክንያቱም በዚያ አካባቢ ውሃ የለም ነበርና እነርሱም ከውሃ ችግር ነፃ ስለሆኑ ደስ አላቸው ለእንግዶችም ታላቅ መስተንግዶ አደረጉ ።

ከዚያም ተነሥተው ግንቦት ፳ ቀን ብርብር ተራራ ደርሰው እድሳትና ጽዳት አስደርገው በማግሥቱ አቡነ አራጋዊ ቤተ መቅደሱን በሜሮን አክብረውና ባርከው በእመቤታችን ድንግል ማርያም ስም የተሰየመችውን ታቦት አስገብተው ቅዳሴ ቤቷን ግንቦት ፳፩ ቀን አክብረዋል በታቦቷም ላይ የተቀረጸው ጽሑፍ ፲ቱ ቃላተ ኦሪትና ፮ ቃላተ ወንጌል ሲሆን እንዲሁም ዛቲ ታቦት ዘወጽአት በዓፄ ገብረ መስቀል ንጉሠ ኢትዮጵያ የሚል በቅዱስ ያሬድ እጅ የተዘጋጀች መሆኗን የሚገልጽ ነው ፣ ንጉሡ ገብረ መስቀልም ለብርብር ማርያም ብዙ ርስት ጉልት ከንዋየ ቅድሳት ጋር ሰጥተዋት በመጡበት እኳኋን ተመልሰዋል ከዚያ ዘመንም ጀምሮ ይህች ታቦት ስእለትን ፈጥና የምትሰማ ተአምረኛ ታቦት መሆኗ ታወቀ ።

የዚችም ተአምረኛ ታቦት ፈጥና ሰሚነቷና ተአምረኛነቷ እየገነነ መጥቶ በታላቁ ንጉሥ በዓጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ቡዳኬባን የሚባል የሃይማኖት ጠላት ተነሥቶ የብርብር ማርያምን ቤተ መቅደስ በእሳት ለማቃጠል ሲሞክር አልቃጠልም ብላ አስቸገረችው ከዳኗ እንዲፈርስ አዞ ከዳኗን ለማፍረስ ከጣራዋ ወጣ ሲል መብረቅ ወርዶ ከሐዲውን ቡዳኬንና ወደጣራው ለመውጣት የሞከረውን አቃጠለችው ቤተ ክርስቲያኗ ግን ሳትቃጠል ቀረች ይላል ዜና ዕንበረሞና ድርሳነ ጽዮን ፣

የዚህንም ዝና ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ ሰምተው ወደብርብር ማርያም ገሥግሠው ሔደው በታቦቷ ከተማፀኑ በኋላ በአካባቢው በሚገኘው ዛፍ በቅርቅሐ እንጨት ጣራዋን ግድግዳዋን ወለሏን በሚገባ አድሰው ሠርተው ጳጳሳቱ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል ቀድሰው ቅዳሴ ቤቷን በጥንቱ የቅዳሴ ቤቷ በዓል ግንቦት ፳፩ ቀን አክብረዋል ንጉሡ ዓፄ ዘርአያዕቆብ በጥንቱ በዓጼ ገብረ መስቀል የተሰጣትን ርስትና ሀብት አድሰው ራሳቸውም ንጉሡ ሌላ ርስት ጉልትና ንዋየ ቅድሳት ሰጥተዋት ደብሯ እንደተከበረች እንድትኖር አድርገዋል ።

ከዚያ ዘመን ጀምሮ በየጊዜው የቶ ገሡ ነገሥታት የተሾሙ ጳጳሳት እየተንከባከቧት በሰላም ስትኖር የጣራዋና የግድግዳዋ ቅርቅሐ ከዘመን ብዛት ስለ አረጀ የቆርቆሮ ከዳን ከቅርብ ዘመን



www.ethiopianorthodox.org

በኋላ ተከድናለች ፤

የመሬቱ ወለል ምንጣፍ ግን በዓጼ ዘርአያዕቆብ እንደተነጠፈ በሰላም ይገኛል እንዲሁም የጣሊያን ፋሽስት ሀገራችን ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን ቤተ ክርስቲያኑን ሊያቃጥል በአርፕላን ቦምብ መላልሶ ቢጥልም እንኳን እየተንከባለለ ወደ መሬት በመውረድ ምንም ጉዳት አላደረሰባትም የዚህችንም ተአምረኛ ታቦት ታሪክ ያጠኑ የውጭ ሀገር ሰዎች በኢትዮጵያ በብዙ ቦታ በድርጅታቸው ስም የርዳታ ድርጅት ሲያቋቁሙ ለብርብር ማርያምም ቤተ ክርስቲያን መርጃ እንዲሆን አንድ የእህል ወፍጮ ተክለው በነፃ ሰጥተዋታል የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮምሽንም ጥንታዊነቷንና የቅርቅሐ ቤተ መቅደስ እርሷ ብቻ መሆኗን በማውሳት በፎቶ አንስቶ በመጽሔት አውጥቷት እስከአሁን በየጽሑፍ መደብር ይገኛል በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምርም በመጽሔትና በሥዕል ታሪክ ይገኛል ።

እንባቢያን ሆይ

እንግዲህ የዚችን ቀዳሚትና ተአምረኛ ታቦት ታሪክ ከዚህ በላይ እንደተመለከታችሁት ጥንታዊትነቷንም በማመን ልናውቃትና ልንጐበኛት ልንከባከባትም ይገባናል በዓሏም የሚከበረው የግንቦት ማርያም ፳፩ ቀን የእስተርእዮ ማርያም የፍልሰታ ኪዳነ ምሕረት ነውና የምንችል በቦታዋ ተገኝተን በዓሏን ብናከብር መልካም ነው በአካባቢዋም ቅረቀሐዎች በብዛት ይገኙባታል ደስ ያሰኛል የብርብር ማርያም ታሪክ ይህንን የመሰለ ሲሆን በሰፊው ለመረዳት የፈለገ ግን የዜና ዕንበረምን ሊቀ ካህናትንና ከአኩስምን ድርሳነ ጽዮን ቢመለከት በሰፊው ለመረዳት ይችላል።

የታሪኩ አቅራቢ
አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ

# ዜና ዕረፍት

## የሠአሊ ሙሉ ጌታ ዕንግዳ አጭር የሕይወት ታሪክ

በሥዕል ሞያ እጅግ በጣም የታወቁት ሙሉ ጌታ ዕንግዳ በጎንደር ሀ/ስብከት ደበረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ ዋንቃት ማርያም ከአባታቸው ቄስ ዕንግዳ ድንገት ከእናታቸው ወ/ሮ ብዙነሽ ቦጋለ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ታህሣሥ ፳፬ ቀን ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በተወለዱበት ደብር ከነበሩት መሪ ጌታ ብርሃኑ ንባብና ዳዊት የቃል ትምህርት ፀዋትወ ዜማ ተማሩ ።



ሠአሊ ሙሉ ጌታ ዕንግዳ እኚህ ነበሩ

ከዚያም ወደ ጋይንት አውራጃ ስማዳ ወረዳ ወደ ደብረ ዕንቁ ማርያም ሒደው ከመምህር ጌጡ ተሰማ ቅኔ ተቀኝተዋል ቅኔ ካወቁ በኋላ ወደ ተወለዱበት ደብር ተመልሰው በዲቁና ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ቆይተው ለአቀመ አዳም ሲደርሱ በሕግ ሚስት አግብተው ትዳር መሥርተዋል ቀደም ሲል ቁም ጽሕፈት ተምረው ስለነበር በትዳር ላይ እያሉ ቀለም አውጥተው ብዕር ቀርጸው ብራና ፍቀው ብዙ መጻሕፍትን ጽፈው ለቤተ ክርስቲያን አበርክተዋል ።

ከብዙው ቁም ጽሕፈታቸው ለቆማ ፋሲለደስ ደብር አንድ መዝገብ ቅዳሴ ጽፈው በነፃ ሰጥተዋል እንዲሁም ለዋንቃት ማርያም ተአምረ ማርያምና ግንዘት ጽፈው በነፃ አበርክተዋል ። ከዚያም በኋላ ወደ ጎጃም ሀ/ስብከት ሒደው በደብረ ማርቆስ ደብር በሥዕል ሞያቸው ከታወቁት ሊቀ አለቃ ማህሌ ዘንድ የሥዕል ትምህርት ለሁለት ዓመታት ያህል ተከታትለው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከትልቅ ወንድማቸው ከበለጠ ዕንግዳ ጋር ተቀምጠው አምኃ ደስታ ት/ቤት ይባል በነበረው ት/ቤት ዘመናዊ ትምህርት ጀምረው እስከ ፰ ድረስ ከተማሩ በኋላ በሥዕል ሥራ ከፍተኛ ውጤት ስላገኙ በባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር በሚመራው በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ጎን በሚገኘው ሥነ ጥበብ ከሚባለው ት/ቤት የሥዕልና የቅርፃ ቅርፅ ሞያ እንዲማሩ ተደረገ በዚያም በሥዕልና በቅርፃቅርፅ ሠልጥነው ዲፕሎም ተቀብለዋል ከዚያም ጀርመን ት/ቤት ገብተው ሲስተር ሚስስ ኢባ ዲተንበርግ ከተባሉት የመንፈሳዊ ሥዕል ባለሞያ መምህር ፮ ዓመት ተምረው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

ሠዓሊ ሙሉ ጌታ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ በሥዕል ሞያ ከታወቁት ሊቅ አለቃ መዝሙር ለሁለት ዓመት ያህል በደንብ ሠልጥነው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ። ከዚህ ሌላ ሰባት ዓይነት ቀለማት ከልዩ ልዩ ዕፀዋት ቀምመውና ተፈላስፈው በማውጣት በተግባር ላይ እንዲውል ለሥነ ጥበብ ት/ቤት አቅርበው የምሥጋና ወረቀት ተቀብለዋል ሽልማትም አግኝተዋል ።

በዚህም ከፍተኛ ዕውቀታቸው የትምህርት ሚንስቴር አዲስ አበባ ከተማ በምሥራቅ አጠቃላይ ት/ቤት መድበ ሥዕል እንዲያስተምሩ ስላደረጋቸው ማስተማር ከጀመሩ ፳ ዓመት ሁኗቸው ነበር ።

ሠዓሊ ሙሉ ጌታ እንግዳ በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም በሰበካ ጉባኤ ተመርጠው ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል:- ሠዕሊ ሙሉ ጌታ የአለቃ መዝሙር ዘዳዊት ረዳት በመሆን በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የጣራና የግድግዳ ሥዕል በጎላ ቅ/ሚካኤል ፤ በጎፋ ቅ/ገብርኤል የነፃ አገልግሎት አበርክተዋል ።

ከዚህ ሌላ ከግል ገንዘባቸው ወጭ በማድረግ ለጎሐ ጽዮን ማርያም ምስለ ፍቅር ወልዳ ለዋሻ ሚካኤል የቅዱስ ሚካኤልን ሥዕል ፤ ለመናገሻ ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳና ሥዕለ ስቅለት ለገነተ ኢየሱስ ሥዕለ ተክለ ሃይማኖት ጎጃም ሀ/ስብከት ለደብረ ማርቆስ ሥዕለ ማርቆስ በነፃ ሥለው አበርክተዋል ።

ሠዓሊ ሙሉ ጌታ እንግዳ በትጉህ ሠራተኝነታቸው ራሳቸውን ከመርዳት አልፈው ወገናቸው ተቸግሮ ያዩ እንደ ሆነ ገንዘብ ከኪሳቸው አውጥተው ለችግረኛው ሰው በመስጠት ከደረሰበት ችግር እንዲላቀቅ ከማድረጋቸውም ሌላ ችግረኛ ሰውም ዘወትር በልመና እንዳይኖር ከችግር የሚድንበትን ዘዴ እስተምረው መክረው በሥራ መስክ በማሰማራት በዙ ሰዎችን የረዱ ቅንና ታማኝ ሰው ነበሩ ።

ሠዓሊ ሙሉ ጌታ ዕንግዳ በሕዝባዊያንና በመንግሥታውያን ድርጅቶችም በትረፍ ጊዜያቸው በልዩ ልዩ ዝግጅት አስተዋጽኦ ስለ አደረጉ ምስጋናና የምስክር ወረቀት ሽልማት ተቀብለዋል ። በመንበረ ፓትርያርኩም ግቢ በሚገኙ የቤተ ክህነት ጽ/ቤቶች በሮች ላይ በድርብ ፊደል የመለያ ስሞችንና ቁጥሮችን በነፃ ሰርተው አበርክተዋል ። ከዚህ ሌላ የበገና ግጥሞችን የበገናን መዛሪያዎቹ ጌጦችን ቀርጸውና ሠርተው ለያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት በነፃ ሰጥተዋል ።

ሠዓሊ ሙሉ ጌታ ስማቸውን የሚያስጠሩ ሦስት ወንዶች ሁለት ሴቶች ልጆችን ከባለቤታቸው ወ/ሮ ነገደ ብርሃኑ ወልደዋል በመጨረሻም በደረሰባቸው ድንገተኛ ህመም ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ገብተው ሲታከሙ ለሰላሳ ቀናት ከቆዩ በኋላ ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ.ም በተወለዱ ፶፱ ዓመታቸው አርፈው በበነጋው ዘመድና ወዳጅ በተገኙበት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት በገነተ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል ።

ሠዓሊ ሙሉ ጌታ እንግዳ ትልቅ ትንሽ ሳይሉ ሰውን ወዳጅና አክባሪ ሽማግሌዎችንና ባልቴቶችን እንደ አባት እናት ትንንሾችን እንደ እህትና ወንድም የሚመለከቱ ሁልጊዜ ደስተኛ አንድ ቀን የማይከፋቸው ነበሩ ያዘነና የተከዘ ሰው ሲያዩ ያንን ለማስደሰት የሚጥሩ ደግ ሰው ነበሩ ፤ ከዚያም የተነሣ በሞቱ ጊዜ የሥራ ጓደኞቻቸው "ሙሉ ጌታ እንግዳ አንድ ቀን ሳይከፋው ያን መሰል ጠባይ ካፈር ቀላቀለው" የሚል ጽፈው ከመቃብራቸው ላይ አስቀምጠውላቸዋል ።

ሠዓሊ ሙሉ ጌታ ዕንግዳ ለአንድ ደቂቃም ቢሆን ሥራ ፈትቶ መቀመጥን የማይወዱ ትጉህና ታታሪ ነበሩ ነገር ግን ኑሮ ኑሮ ከመሬት ዞሮ ዞሮ ከቤት እንደሚባለው እግዚአብሔር በዚህ ዓለም እንዲኖሩ የፈቀደላቸውን ዘመን ፈጽመው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። ቢሆንም ሞት ሁሉንም በተራ የሚያዳርስ በመሆኑ ለቤተ ሰቦቻቸው መጽናናትን ለነፍሳቸው መንግሥተ ሰማያትን እንዲያወርሳቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ወደ እግዚአብሔር ትማፀናለች ።

የዜናው አቅራቢ
አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በአሁኑ ጊዜ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በየአቅጣጫው የምታደርገው የልማት እንቅስቃሴ እጅግ በጣም የሚያስመሰግን ነው ። ካህናት የትርፍ ጊዜያቸውን በከንቱ እንዳያባክኑ እየቀደሱ እንዲሠሩ ፤ እየሠሩም እንዲቀድሱ ለማድረግ አመች በሆኑት የቤተ ክርስቲያን አካባቢዎች ሁሉ የልማት እንቅስቃሴ እየተካሄደ ነው ።

በቤተ ክርስቲያን ለሚደረጉትም የልማት እንቅስቃሴዎች የበላይ ሆነው መመሪያ የሚሰጡት በአንደኛ ደረጃ የሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሀ/ስብከቱ ሊቃነ ካህናት ናቸው ፤ የአውራጃዎችና የወረዳዎች ሊቃነ ካህናትና ካህናት የሰበካ ጉባኤ ተመራጮችም ለልማቱ ተግባር ተባባሪዎች ሆነው የመሥራት መንፈሳዊ ግዴታ አለባቸው ።

በየአብያተ ክርስቲያኑ ለሚደረገው የልማት ተግባር ጠንክረው በመሥራት የተመሰገነ የሥራ ፍሬ ያሳዩ በርካታ ያሉ ናቸው በዚሁ መነሻነት ለመግለጽ የምንፈልገው በወለጋ ሀ/ስብከት በአሶሳ አውራጃ በስብከተ ወንጌልና የሥራ መሪነት ከ፲፱፻፸፫ እስከ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም የተፈጸመውን የአብያተ ክርስቲያናት የሥራ ፍሬ ነው ።

ጽሑፉን የላኩልን የዚሁ አውራጃ ሊቀ ካህናት መልአከ ኃይል እንየው ውቤ ናቸው መልአከ ኃይል የተፈጸመውን የሥራ ፍሬ እንደሚከተለው በዝርዝር አቅርበውታል ።

፩ኛ/ ቀደም ሲል በ፲፱፻፸፩ ዓ.ም በተቋቋሙት የ፲፬ ሠፈራ ጣቢያዎች አብያተ ክርስቲያናት ቀደም ብለው ከነበሩት ፪ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በድምሩ በ፲፮ አብያተ ክርስቲያናት የእርሻና የወተት ፳፮ የቀንድ ከብቶች አስገዝቶ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ በማደል በሬዎች በእርሻ ላይ ላሞችም ወተትን በመስጠትና ጥጆችን እየወለዱ በማሳደግ ላይ ይገኛሉ ።

፪ኛ/ ወደ እርሻ ውጤት መለስ ብለን ስንመለከት ደግሞ በቆሎ ፤ ማሽላ ፤ ኑግ፤ ጤፍ ፤ ስንዴ ፤ የመሳሰሉትም ሁሉ በብዛት ስለተመረቱ በቅርብ ቀን ለገበያ ሽያጭ ይቀርባሉ ።

፫ኛ/ አትክልትን በሚመለከት ስለ አትክልት አተካከል ከዚህ ቀደም ከዚሁ መሥሪያ ቤት የሔዱ ልዑካን





www.ethiopianorthodox.org

እንደ ተመለከቱት ሁሉ በዚሁ አውራጃ የአትክልት ዓይነት በአንደኛ ደረጃ ማንጎ የሚባለው ተክል ስለሆነ በየአብያተ ክርስቲያናቱ በብዛት ለምቶ ይገኛል ። ከ፫ ዓመት በኋላ የዚሁን ተክል ምርት በብዛት ለገቢያ የምናቀርብ መሆናችንን አረጋግጣለሁ የጌሾ የባሕር ዛፍ የጥድ የአርዘ ሊባኖስ አትክልቶች በተጨማሪ ተተክለዋል ።

መልአከ ኃይል እንየው ውቤ ፤ የሠሩትና የሚሰሩት የልማት ተግባር ለሌሎች በአርያነት ሊጠቀስ የሚችል ዓቢይ ቁም ነገር ነው ፤ የቤተ ክርስቲያናችን አባል የሆነ ሁሉ አባልነቱን ማረጋገጥና ማስመስከር ያለበት ለቤተ ክርስቲያን በሚሠራው መልካም ተግባር መሆን አለበት ።

ቤተ ክርስቲያናችን ለልማት ተግባር እንግዳ ባትሆንም በየአብያተ ክርስቲያኑ አካባቢ የሚከናወኑት የልማት እንቅስቃሴዎች ሁሉ በተሐድሶ ጉዞ ላይ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያናችን ብሩህ ተስፋን የሚያጐናጽፉ ናቸው ።

በምድር ላይ ለተወሰነ ጊዜ እንዲኖር የተፈጠረ ሰው ሁሉ የሚኖርባትን መሬት ማበጀት መጠበቅ ይኖርበታል ።

ለአዝርእትና ለአትክልት ፤ የሚስማሙ ብዙ ገዳማት አድባራት ይገኛሉ ግን እስከ አሁን ድረስ የልማት ተግባር አልተጀመረባቸውም ሠርተው ራሳቸውን ለመቻልና ሌላውንም ለመርዳት የሚችሉ አንዳንድ ካህናት ከሥራ ጽሩዓን ሆነው ይገኛሉ በየአህጉረ ስብከቱ የተመደቡ ሊቃነ ካህናት የሰበካ ጉባኤ ተመራጮች እንደነዚህ ያሉትን ወገኖች የመመልከትና በየችሎታቸው ሠርተው እንዲበሉ የመመደብ ሐላፊነት አለባቸው ።

መልአከ ኃይል እንየው ውቤ ፤ የአሦሳ አውራጃ ሊቀ ክህናት ከመሆናቸውም ሌላ እየተዘዋወሩ የስብከት ውንጌሉንም ተግባር የሚያከናውኑት ራሳቸው ናቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም እንዲታነፁ አድርገዋል ። በየአቅጣጫው የሠሩትና የሚያሠሩቱ ሥራ ሁሉ ለሌላው በአርአያነት የሚመጠቀስ ነው በየአህጉረ ስብከት በአውርጃዎችና በወረዳዎች የተመደባችሁ ሊቃነ ካህናት ሁሉ ፤ በስብከተ ወንጌልም በቢሮ ሥራም በልማትም የምታደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ እንደ መልአከ ኃይል የተመሰገነ እንዲሆን በርትታችሁ ሥሩ በማልተ መንፈሳዊ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን ።

ከመልአከ ኃይል እንየው

ውቤ

# ስብከተ ወንጌል

ክፍል ስድስት

አማኞች ክብር ለሚገባ ክብርን የሚሰጡ ግብርን መክፈል ለሚያስፈልገው ግብርን የሚከፍሉ ለቤተ ክርስቲያንም አስራት በኩራት አስተዋጽኦ የሚያደርጉት ወንጌል ሲሰበከላቸው ነው ። ከስተትም የሚታረሙት ባልንጀሮቻቸውንም እንደራሳቸው አድርገው የሚወዱት ክፉውን በክፉ ሳይሆን በመልካም ተቃውመው የሚያሸንፉት በየጊዜው የወንጌል ስብከት ሲሰበከላቸው ነው ። በጠቅላላው ሀገር ደኅንነትን ሕዝብ ሰላምን አግኝቶ ሁሉም ወደ ሥራ ዓለም የሚሰማራው ህይወቱ በትምህርት ሲስተካከል ነው ። ይህ ከሆነ ብዙ የተሰጣቸው ብዙ ይከፍላሉ በጥቂት የታመኑ በብዙ ሊታመኑ ይችላሉ። ስብከተ ወንጌልን እየተማሩና በመንጌል ትምህርት ታንጸው ያደጉ አማኞችም በምግባር ፣ በሃይማኖት ያደጉ ብቻ ሳይሆኑ እርስ በርስ በመፋቀርና በማህበራዊ ኑሮ ተባብረው ስለሚሠሩ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለሀገርም ለቤተክርስቲያንም ዕድገትን ያተርፋሉ ።

ይህ ብቻ አይደለም በሀገርም ላይ መከራ ቢመጣ ጠላት ቢነሳ ሀብታቸውን ንብረታቸውን ህይወታቸውንም ጨምሮ መስዋዕት አድርገው ያቀርባሉ ይህም በተፈጸሙት ፈተናዎች ተመስክሯል ። የሀገሪቱ መብት እንዲከበርና የቤተ ክርስቲያኗም ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ ታላቅ ተጋድሎ ከማድረጋቸውም በላይ ከእነሱ የቀደሙት አባቶች በሰሩት መሰረት ላይ በሥራቸው አዳዲስ የሥራ ግንብ ገነቡ እንጂ ዝም ብለው አልተመለከቱም ይህንንም ለማወቅ ብንፈልግ በአስራ አንደኛውና በአሥራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን የተፈጸሙትን ተግባሮችና ደክሞ የነበረው ስብከተ ወንጌል ኃይል አግኝቶ እንደተስፋፋ በሚከተሉት መስመሮች በተራ እናቀርባለን ።

ለወንጌል ማስተማሪያና ለአገልግሎት መስጫ እንዲሆኑ በሀገሪቱ የተሰሩት አድባራትና ገዳማት በተለይም በላሊበላ ዘመነ መንግሥት ከድንጋይ ቋጥኝ ተፈልፍለው የተሰሩት አስራ አንድ አብያተ ክርስቲያናት የስብከተ ወንጌል ውጤቶች ናቸው ። እነዚህም የሚገኙት በወሎ ክፍለ ሀገር ላስታ በሚባለው አውራጃ ነው ላሊበላ ብዙዎች አዋቂዎች ሠራተኞችን ሰብስቦ ግሩም በሆነ አሰራር ያሰራቸው አስራ አንድ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ። እነዚህም በሙሉ ከአለትና ከቋጥኝ የተዋቀሩና የተፈለፈሉ ናቸው ። ወለላቸውም ጣራቸውም ግርግዳቸውም መስኮታቸውም ፤ መዝጊያቸውም ሁሉ ከድንጋይ የተጠረበ ነው ። በእያንዳንዱም ቤተ ክርስቲያን ግርግዳ አምድ ላይ የወንጌልን ቃል የሚያስተምርና የክርስትና እምነትን የሚያስታውስ ምልክት ይታይበታል በተጨማሪም ቤተ መድኃኔዓለም ፤ ቤተ መስቀል ፤ ቤተ ደናግል ቤተ ማርያም በሚሉ ስሞች የተሰየሙ ህንፃዎች አሉ ። እነዚህም ብዙ ጎብኚዎችን ይስባሉ ። ያሉበትም ሥፍራ በአሰሪው ስም ተሰይመው ደብረ ገሊላ ወይም ላሊበላ ተብለው ይጠራል ።

አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ላሊበላ አንድ ወጥ የሆኑትንና ከቋጥኝ ተፈልፍለው የተሰሩትን የቤተ ክርስቲያን ህንፃዎች የክርስትና ሐይማኖት መዲና የሆነችውን ኢየሩሳሌምን በኢትዮጵያ ውስጥ ለመድገም የታቀደ የመልካም ሥራ ውጤት ነው ብለውታል ። ይህንንም ሲያብራሩ በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ምዕመናን ኢየሩሳሌምን ለመሳለም በእግራቸው ያደርጉት የነበረው ጉዞ እጅግ አድካሚ ከመሆኑም ሌላ በየመንገዱ አረማውያን ከሚፈጸሙባቸው የሞት አደጋ ለማዳን ፤ ከድካምም ለማረፍ ሲሆን በአጠቃላይ የአማኞች መናኸሪያ የሆነችው ኢየሩሳሌምን በዚህ በተሰራው በአዲስ ህንፃ ቤተ ክርስቲያን ለመተካት ታስቦ ነው ። በተጨማሪም ለመሳለም ለሚመጡትና ጉብኝት ለሚያደርጉት ሁሉ የወንጌል ትምህርት ለማስተማር ቦታው ምቹ መሆኑ ታምኖበት ነው ይላሉ ። እርግጥም በዚያ በጨለማ ዘመን ብዙ ምዕመናን ለመሳለምና አያሌ ጎብኝዎችም ጉብኝት ለማድረግ ወደዚህ ቦታ በብዛት ይጎርፉ ስለነበር ወንጌልን ለማስተማር ምቹ ሥፍራ ሆኖ በመገኘቱ በርከት ያሉ አማኞች በወንጌል ትምህርት ለመጠቀም ችለዋል ።

ስብከተ ወንጌል የተስፋፋዉና ቤተ ክርስቲያንም ይህን ያህል ዕድገት ያገኘችው ምዕመናንም ሊበዙ የቻሉት ብርሃናቸው በሰው ፊት የሚያበራና የጨለማ ከዋክብት የሆኑ የወንጌል መምህራን በመገኘታቸው ነው ። ከነዚህም መካከል የደብረ ሊባኖስ ገዳም መስራች የሆኑት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ይገኙበታል እኚህም አዲስ ሐዋርያ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት በደብረ አሰቦ ስብከተ ወንጌል አቋቁመው ሁለት መቶ ካህናት ለማሰልጠን ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ። ከነዚህም መካከል አርባው መነኮሳት ሲሆኑ ስልሳው ቀሳውስት ነበሩ ። መቶው ግን ዲያቆናት መዘምራን ናቸው እነዚህ ሁሉ በስብከተ ወንጌል ከሰለጠኑ በኋላ ከአርባው አስራ ሁለቱን ንቡራነ ዕድ ብለው ሹመው በየአውራጃው ወንጌል እንዲያስተምሩ ላኩዋቸው ። የቀሩት ደግሞ በየወረዳው ወንጌልን እንዲያስተምሩ አደረጓቸው ። የቀሩት ደግሞ በየወረዳውና በየቀበሌው ወንጌል እንዲያስተምሩ ሰደዱዋቸው ዛሬም ቢሆን ይህ ሥነ ሥርዓት በትውፊት ሲያያዝ መጥቶ ከደብረ ሊባኖስ መነኮሳት መካከል በየጊዜው አስራ ሁለት ለምርፋቅ ሹምነት ተመርጠው የገዳሙን አስተዳደር በጠቅላላ ይመራሉ ይጸልያሉ ያጸልያሉ ወንጌልንም ይሰብካሉ ።

ወደ ርዕስ ነገራችን እንመለስና በዚያን ዘመን ስብከተ ወንጌል በጣም ተስፋፍቶ ነበር ምክንያቱም ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት የሥራ ሰው ከመሆናቸውም የተነሳ ይኩኖ አምላክን ቀብተው በማንገሣቸው ለቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የሚሆን ሲሶ መንግሥት (አስራት በኩራት)አገኙ ። ስለ ሲሶ መንግሥት አሰጣጥ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወ/ሥላሴ ዋዜማ ብለው በሰየምት የታሪክ መጽሐፋቸው ከይኩኖ አምላክ እስከ ሰርጸ ድንግል በሚለው ክፍል በገጽ ፴፱ ሲተርኩት ፤

በዩዲት መንግሥት አርባ ዓመት በ፲፮ ወገኖች መንግሥታት ፲፱፻፴፫ ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ርስትና ጉልት ሁሉ በመንግሥት እጅ ሆኖ ነበርና ነአኩቶ ለአብ መንግሥቱን ለይኩኖ አምላክ ሲያስረክብ የቤተክርስቲያን ንም ርስትና በዘመኑ የበላይ ተጠሪነት ለነበራቸው ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሲሶ መንግሥት ተሰጡ ሲሉ ጽፈዋል ። ወንጌልን ያስተማሯቸው ተማሪዎች በሥራቸው ስለተባበሩዋቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖት ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋና አምልኮ ጣዖት እንዲጠፋ ቤተ ክርስቲያን እንድትገለገልና የካህናት ኑሮ እንዲሻሻል የተቀበሉትን ሲሶ መንግሥት በሚከተለው ሁኔታ ከሥራ ላይ እንዲውል አደረጉ ፤ አንደኛ፡ ለስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ሁለተኛ፡ ለሊቃውንትና ለመምህራን ሦስተኛ ፤ ለቀዳስያንና ለመዘምራን አራተኛ ፤ በገዳማት ለሚገኙ መነኮሳት ድርጎ ፤ አምስተኛ ፣ ለችግረኞች መርጃ የሚሆን አከፋፍለው ይረዱበት ነበር ። ይህም በመሆኑ ስብከተ ወንጌል ሊስፋፋ ከመቻሉም ሌላ የቤተክርስቲያን አገልግሎትና የካህናት ኑሮ ተሐድሶ አግኝቶአል ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ስለ ሲሶ መንግሥት ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል በሚለው በሦስተኛ የታሪክ ዕትማቸው በገጽ ፷፩ የሰጡትን አስተያየት ስንመለከት "ይኩኖ አምላክ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት በምታስገብርበት ሲሶ መንግሥትና ከዚህም በቀር በየሐብታሙ በስለት ፤ በስጦታ ፤ በምታገኘው ሀብት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሀብታም ሆነች ከዚህም የተነሳ በአገልግሎት የተሰማሩት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሠራተኞች ቁጥር በቤተ መንግሥት ከሚያገለግለው ሠራተኛ ይልቅ በልጦ ተገኝቷል በተጨማሪም በየገዳማቱ ፤ በየአድባራቱ ፡ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ከየሐገሩ ከየመንደሩ የሚመጣላቸውን ተማሪ የሚያስተምሩ መምህራን በረከቱ ስለዚህ የሐብት አሰባሰብና አያያዝ በደንብ ካለመከናወኑም ሌላ በዚህ በሲሶ መንግሥት አባል ቤተ ክርስቲያን የተጠጋ ሁሉ እንደየአቅሙ ስለሚተዳደርበትና ጠንካራ ተቆጣጣሪም ስለሌለበት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ካረፉ በኋላ ስብከተ ወንጌል እየደከመ መሄድ ጀመረ ።

ይህ ሊሆን የቻለው በቤተ ክርስቲያን የሚተዳደረው ካህን የያዘውን ከማጽናት ወይንም መንፈሳዊ ትምህርቱን ዜማውን ቅኔውን ብሉይና ሐዲሱን ሁሉም እንደችሎታው ከመማር ከማስተማር ከመመራመር በቀር ከአለበት ሥፍራ አለፍ ብሎ ስብከተ ወንጌልን ለማስተማር ለማጥመቅ ልፋጠን የሚል ለሐዋርያዊ ተልዕኮ የሚተጋ መምህርና ቄስ በልክ መሆኑን ዘርዝረውታል" እነሱም ቢሆኑ በተተከሉበት ቤተ ክርስቲያን ካልሆነ ተዘዋውረው አገልግሎት አይሰጡም ነበር ብለዋል ።

እንዳሉትም ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋና ምዕመናን እንዲበረክቱ ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ከተፈለገ በተራራ





www.ethiopianorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ሕይወት

በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩ ምእመናን ቤተ ክርስቲያን በተለያየ ሁኔታ ይፔዳሉ ይህም ሲባል በልማድና በወግ ፡ ሰዎች ሲሄዱ አይተው ሌሎችም ዝማሬው መዝሙሩ ደስ ብሏቸው ሲሄዱ የቀሩት ደግሞ በአላማ ማለትም በጸሎት ከአምላካቸው ተገናኝተው የኃጢአት ሥርየት አግኝተው በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስ ለመታደል ይጓዛሉ ። ነገር ግን በልማድ የሚጓዙት ክርስቲያናዊ ጉዞ መነሻና መድረሻ እንደሌለው ሁሉ በሕይወታቸው እድገት አያሳዩም መንፈሳዊ ዓላማ ያለው ክርስቲያን ግን በመጀመሪያ የቤተ ክርስቲያ

ላይ ያለች ከተማ ለሁሉ ግልጥ ሆና ለሁሉ ትታያለች እንጂ አትሰወርም መብራትም አብርተው በመቅረዝ ላይ ከማስቀመጥ በቀር እንዳይታይ ከእንቅብ በታች አያስቀምጡትም ። ቤተክርስቲያንም የወንጌል ብርሃን የሚበራባት መቅረዝ ስለሆነች የወንጌል ብርሃን እንዲያበራ ስብከተ ወንጌሉን ማጠናከር ይገባታል ካህናትም ተዘዋውረው ማስተማር ይፈለግባቸዋል ። ክርስቶስም ሲያስተምር እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የህይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሏል ። የዮሐንስ ወንጌል ም·፰ ፡ ቁ ፲፪

ህይወታችን በጨለማና በችግር በሚጓዝበት ጊዜ ክርስቶስ ሁል ጊዜ በፊታችን ይሄዳል ፍለጋውንም ከተከተልን መንገዱን እያሳየ የወንጌልን ብርሃን ያበራልናል ። በጣም ሲጨልምና መንገዱ ሲጠፋብን ደግሞ እርሱ ብርሐናችን ነው ። ስለዚህ የወንጌል መምህራን የሆን ሁሉ እናንተ የዓለም ብርሃናችሁ ተብለናልና የወንጌልን ብርሃን ለሁሉ እናብራ ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

ንን ሕይወት ገምግሞ መረዳት አለበት ይኸውም ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ መጀመሪያ ደብተራ ኦሪት ኋላም ቤተ መቅደስ በዘመነ ሀዲስ ቤተ ክርስቲያን ተብላለች ።

በዘመነ ኦሪት መሥዋዕት ሠውተው ጸሎት ጸልየው ከደዌ ሥጋ ይድኑበት ነበረ በተጨማሪም ኃይለ እግዚአብሔርን ረስቶ በክንዱ በኃይሉ አንፃር ደግሞ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉ እንደማይገባቸው ሆነው ሲገኙ የተቀሠፉበትም ወቅት እንደነበረ በቅዱስ መጽሐፍ እናነባለን ።

በመጽሐፈ ሳሙ· ቀዳ· ፪ ቁ፲፪ ጀምሮ እንደምናነበው የሊቀ ካህናት ዔሊ ልጆች ፈሪሀ እግዚአብሔር ስላልነበራቸው በመቅደስ ፊት የሚበድሉትን በደል እየሰማ በአግባቡ ባለመገሠፁ አምላኩ ተቆጣ ታላቅ መአት በላዩ ላይ አመጣ ይኸውም እስራኤላውያንና ፍልስጥኤማውያን ስምምነት ስላልነበራቸው በዚህ ወቅት ጦርነት ተነስቶ ነበረ በም· ፬ ላይ እንደምናነበው በጦርነቱ የቃል ኪዳን ታቦቱና ሁለቱም የዔሊ ልጆች አብረው ዘምተው ነበረ ነገር ግን በበደላቸው ምክንያት በጦርነቱ ድል ተመቱ የዔሊም ልጆች በዚያው ሞቱ ታቦቷም ተማረከች እርሱም የዚህን ወሬ ሲሰማ ከወንበሩ ተገልብጦ ሞተ ይላል በኦሪት ዘዳግም እንዲህ የሚል ቃል እናነባለን ።

ለአንተ በምትጠራበት በአምላክህ በእግዚአብሔር መሠዊያ አጠገብ ከማናቸውም ዛፍ የማምለኪያ አፀድ አድርገህ አትትከል አምላክህ እግዚአብሔርም የሚጠላውን ሃውልት ለአንተ አታቁም ። ዘዳ·፲፮ ፡፳፩

ስለዚህ በእግዚአብሔር መቅደስ ፊት ስንቆም አቅማችን በፈቀደ መጠን ከማናቸውም ፈጣሪያችንን ከሚያሳዝኑ ነገሮች ራሳችንን ማንፃት አለብን በልቡናችንም ተተክለው ያሉ የተንኰል አፀዶች ማለትም ጣዖት አምልኮ ፡ ስስት ፡ ፍቅረ ንዋይ ዝሙት ወዘተ የመሳሰሉትን ባዕድ አምልኮ ማስወገድ ይገባናል።


ከዚህ ነገር የምንነፃ ከሆንን ግን በዚች ቤት የኛ ልመና ወደ እግዚአብሔር የአምላካችንም ቸርነትና ፀጋ ወደኛ ይትረፈረፍልናል ይበዛልናልም።

አምላክህ እግዚአብሔር ሊያድንህ ጠላቶችህንም በእጅህ አሣልፎ ሊሠጥህ እንዳይመለስ ሠፈርህ የተቀደሠ ይሁን ይላል ዘዳ ፳፫ ፡ ፲፬-፲፭

እንግዲህ ሰው ቦታውን ይቀድሳል ቦታ ደግሞ ሰውን (ቤተ ክርስቲያናችንን) ለመቅደስ እራሳችንን የተቀደስን ሆነን መገኘት ይኖርብናል ።

በ፫፻፳፭ ዓ·ም· አርዮስ ኢየሱስን አምላካዊ ፍጡር የሆነ ከእግዚአብሔር ያነሰ ነው ብሎ አስተማረ በዚህ የጉባኤው ሰብሳቢ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ አፈ ጉባኤው ቅዱስ አትናቴዎስ ከ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጋር በኒቅያ ተሰብስበው እግዚአብሔር ወልድ ጥንት የተወለደ እንጂ ፍጡር አይደለም በመለኮታዊ ባህርዩ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ ነው ብለው አርዮስን አወገዙት (ንዜኑ ህላዌሁ ለአብ ምስለ ወልዱ ወህለዌሁ ለወልድ ምስለ አቡሁ ቅዳ ሠለ ምዕ የቀናው ሃይማኖት እንዲታወቅም ሊቃውንቱ የሃይማኖት ጸሎት ደረሡ ።

በተጨማሪም በ፫፻፹፩እ·ኤ·አ· ጉባኤው የእንጾኪያው ሊቀ ጳጳሳት ሜልጥዮስ ከ፻፶ሊቃውንት ጋር በቁስጥንጥንያ የተሰበሰቡበት ምክንያቱም የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳት መቅዶንዮስ መንፈስ ቅዱስ አብና የወልድ ባህርየ መለኮትን ተሳታፊ አይደለም እንደ ሊቀ መላዕክት ያህል ነው ብሎ አስተማረ ሊቃውንቱም ከኒቅያ ውሳኔ ሃይማኖት መጨረሻ ላይ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን እርሱም ጌታ ህይወትን የሚሰጥ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት የሚሰገድለትና የሚመሰገን ነው ብለው የመንፈስ ቅዱስን ነገር አጉልተው አስተማሩ መቅዶንዮስንም አውግዘው ለዩ እንግዲህ ለምሳሌ ያህል እነዚህን ጠቀስኩ እንጂ በየዘመኑ ሁሉ አንድ ባህርይ የምትል ቤተ ክርስቲያናችን የተለያዩ መናፍቃን ተነስተውበት ትምህርቷንና እምነቷን ለመለወጥ ሙከራ አድርገው ነበረ ሆኖም ትምህርታቸውን ውድቅና እነርሱም ከአፈር በታች ሲውሉ ተዋህዶ እምነታችንና ቤተ ክርስቲያናችን ግን ዛሬም በሕይወት አለች እስከ ዓለም ፍፃሜም በአምላኳ ጥበቃ ትኖራለች ።



ነገር ግን በዘመናችንም ብዙ አርዮሳውያን እንዳሉ ማወቅ አለብን አርዮሳውያን እንደ ርግብ የዋህ መስለው በውስጥ እንደ እባብ የሚናደፉ ብዙ የሃይማኖት መሰል ድርጅቶች በተለያየ መንገድ ወደዚች ወደ ቀናች ወደ ጸናች ሃይማኖት እየሾለኩ እየመጡ ናቸው ስለዚህ የነዚህን ስሁታን ሁኔታ የተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆችና አማኞች ተረድተን ቤተ ክርስቲያናችን መቼ እንደተመሠረተች ያሳለፈቻቸውና የተጓዘችውን ምዕራፍ ጠንቅቀን መረዳት ይኖርብናል ይህ ካልሆን ግን በነዚህ ሲያዩዋቸው ማር ውስጣቸው እሬት በሆኑ አስመሳዮች ተጠልፈን እንወሰዳለን ማለት ነው በተለይ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ስንሰበሰብ ደርሶ መመለስና መዝሙር መዘመር ብቻ ሳይሆን ጠለቅ ብለን ታሪክን ከአባቶች መምህራንና ከቅዱሳት መጻሕፍት መርምረን አውቀን እኛንም ሆነ ሌላውን ክርስቲያን በመናፍቅ ከመነጠቅ ለማዳን እንችላለን ቤተ ክርስቲያን ስንል ደግሞ ህንፃውን ብቻ አይደለም በማደሪያው አዳሪው ፤ በአዳሪው ማህደሩ መጠራት ልማድ ስለሆነ በክርስቲያን ማህበር መሰብሰቢያ ቤቱ ቤተ ክርስቲያን ተብሏል ።

ዲ· ስንታየሁ ሥሜ

# የዓለም አብዮተ...

ከገጽ ፳፱ የዞረ

ች) አሳትመው አውጥተዋል ይህም "የካይሮስ ደኩሜንት" በመባል የታወቀ ነው ።

እ.ጎ.ቀ. መስከረም 1985 ታትሞ በወጣው የካይሮስ ዶክሜንት በሰጠው ትንታኔ በደቡብ አፍሪካ ውስጥና ከደቡብ አፍሪካ ውጭ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ስለ ነፃነት ፍትሕና ሰላም የሚደረገውን ትግል እንዲደግፉ አንድ ታላቅ ጥሪ አቅርቦላቸዋል ።

በቅርቡ የወጣው "የሐዋርያነት ምስክር" የተሰኘው ዶክሜንት ልዩ ልዩ እምነቶችና ሐዋርያዊ ተልዕኮ ያላቸው ሁሉ በአንድነት በመሠለፍ ለማኅበራዊ ፍትሕ ትግል እንዲያደርጉ ጥሪውን አቅርቧል ።

በአሁኑ ጊዜም በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ራሳቸውን እንደ አንድ ብሔራዊ መዋቅር በማድረግ ለነፃነት ፣ ለፍትሕ በዘረኝነት ሥር ለሚማቅቁት ጥቁር አፍሪካውያን ቤተሰቦች ተጨባጭ የሆነ ዕርዳታ በማድረግ ትግላቸውን በበለጠ እንዲያጠናክሩ በመረዳት ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚታየው ሁኔታ በአመራር ላይ ያሉት የመንግሥት አካላትና ሌሎችም የማኅበራዊ ክፍሎች ሁሉ ራሳቸውና ድርጅቶቻቸው ጭምር ሳይቀሩ ከዘረኛው መንግሥት ሆነ ተብሎ በሚደረገው የከፋፍለህ ግዛ ዘመቻ አቋማቸው እየተዳከመና እየተፍረከረከ በመሄድ ላይ ይገኛሉ ። ይህም የሚያመለክተው የዘረኛውን መንግሥት የሥልጣን ዘመን በቅርቡ እንደሚያከትም ነው ።

ከኃይሌ አስፋው





www.ethiopianorthodox.org

# መድኃኔ ዓለም

ለብዙ ዘመናት በጽኑዕ ደዌ ተይዞ ሲሰቃይ የኖረ ሰው አንድ ቀን ሙሉ ጤንነትን አግኝቶ በዳነ ጊዜ የደስታውን ብዛት ይህ ነው ብሎ ለመገመት አይቻልም ከመዳኑም በፊት እንኳ "አይዞህ ትድናለህ" ቢሉት በተስፋ ደስ ይለዋል ።

የመጀመሪያው ሰው አዳም የፈጣሪውን ሕግና ትእዛዝ በመተላለፉ በደዌ ኃጢአት ተይዞ ፣ በሲኦል ፣ ጨለማ ተውጦ ፣ በጠላቱ በዲያብሎስ ግዛት ተረግጦ እንዲኖር ከነልጅ ልጁ ተፈርዶበት ነበር ። ነገር ግን ፈጣሪ ለፍጡሩ ርኅሩኅ እንደመሆኑ "ከዘመን በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ" የሚል ቃል ገብቶለት ስለነበር ይህንኑ የተስፋ ቃል ሲጠባበቅ ኖሮ ቀኑ ሲደርስ እውነተኛውን መድኃኒት አግኝቶ ለመዳን በቃ ። እሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው አዳኝነቱም ለመላው ዓለም በመሆኑ መድኃኔ ዓለም የዓለም መድኃኒት) ተብሏል ።

ይህንንም በአዳም ምክንያት ወደዓለም የገባውን ኃጢአት በየጊዜው የተነሡ ደጋግ አባቶችና ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ፣ በሞቱና በትንሣኤውም ዓለም ያድናል ፡ እያሉ ትንቢት ከመናገር በስተቀር ፣ በጾም በጸሎትና በትሩፋት ሊያስወግዱት አልቻሉም "እርሱ ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ፣ ስለበደላችንም ደቀቀ ፣ የደኅንነታችንም ተግሳጽ በእሱ ላይ አኖረ ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈውስን" ሲል ኢሳ ፶፫ ቁ ፭ ነቢዩ አስቀድሞ በትንቢቱ እንደተናገረው በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ዓለም ዳነ ።

ቅጣት የሚገባው ሕግ ላፈረሰ ሲሆን እሱ በሕገ ወጥ ሰው (አዳም) እግር ገብቶ ታሠረ ፣ ተገረፈ ፣ ተሰቀለ ፣ ሞተ ቀድሞ በሔዋን ልብ ገብቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያስፈረሰ ሰይጣን ዳግመኛ በይሁዳ ልብ አድሮ ፈጣሪውን በገንዘብ እንዲሸጥ አደረገ (ለዋጋየ ፴ ብር መዘኑ) የተባለውም ተፈጸመ የካህናት አለቆች እና ሽማግሌዎች ስለክርስቶስ የተነገረውን ትንቢት እራሳቸው እያስተማሩ ቃሉም በዘመኑ ተፈጽሞ ፣ እርሱም የሚያስተምረውን ትምህርት እየሰሙ የሚያደርገውንም ታምራት እያዩ አልተቀበሉትም ። ምክንያቱም በትምህርቱ ፣ በተአምራቱና በሥልጣኑ ስለሚበልጣቸው ጥቅማቸውና ክብራቸው የተቀነሰ ስለመሰላቸው በቅናትና በምቀኝነት ተነሳስተው ያላደረጉት ተንኮል ያልፈጸሙት በደል የለም ። ግማሾቹ ከሳሾች ግማሾቹም ምስክሮች ሌሎቹም ከጲላጦስ ጋር ፈራጆች ሆኑ በክሳቸውም ላይ እንደወንጀለኛ የቆጠሩቸው በሰንበት ሕሙማንን ፈውሷል ፤ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሏል ፣ ቤተ መቅደስንም አፍርሼ በሦስት ቀን እሠራለሁ ብሏል የሚሉ ነበሩ ። ጲላጦስም ነገሩን ከመረመረ በኋላ ለሞት የሚያበቃ ቀርቶ ለእሥራትም የሚያደርስ ምክንያት ባለማግኘቱ "እኔ አንዲት በደል እንኳ አላገኘሁበትም ንጉሣችሁን ፡ እንዴት ልስቀለው ቢላቸው እኛ ከቄሳር በቀር ንጉሥ የለንም ስቀለው ስቀለው እያሉ ጩኸታቸውን አስተጋቡ ፣ ጲላጦስም ከባድ ብጥብጥ መሆኑን ባየ ጊዜ ግራ ገባው ፣ በተለይ ሚስቱ "በሕልሜ ከፉ ነገር አይቻለሁና በዚያ በጻድቅ ሰው ላይ አንዳች ነገር አታድርስ" ብላ የላከችበት መልእክት ልቡን ቢነካውም ፣ ጸብና ክርክር እየበዛ ከመሄድ በስተቀርም የሚያዘልቅ ነገር እንደሌለ አስቦ "ንሥአ ማየ ወተሐጽበ እዴሁ በቅድሜሆሙ ለሕዝብ እንዘ ይብል ንጹሕ አነ እምደሙ ለዝ ብእሲ (እኔ ከዚህ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ) በማለት በሕዝብ ፊት ውሃ አምጥቶ እጁን ታጠበ ከሹመቴ ያሽሩኛል ከሥልጣኔ ያወርደኛል በማለት ሊፈርድለት ሲችል ፈረደበት "ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ" የሚል ጽሑፍ ጽፎ በመስቀሉ አናት ላይ እንዲለጠፍ አድርጎ አምላክነቱን መሰከረ እንጂ ስለ እውነት ፈርጆ ላድነው አላለም ።



ንጹሐ ባሕርይ አምላክ እንደወንጀለኞች ታስረ ተገረፈ ፣ ከሁሉም ይልቅ የሚያሳዝነው አይሁድ በሕጋቸው የተገረፈ አይሰቀልም የሚሰቀልም አይገረፍም ነበር በእርሱ ላይ ግን ያለ ሕግ ስፍር ቁጥር የሌለው ግርፋትና የስቅላት ሞት ፈረዱበት ለተራበ ምግብ ለተጠሙ መጠጥ ሲሆን በመስቀሉ ላይ ሆኖ "ጸማእኩ (ተጠማሁ) ባለ ጊዜ ሆምጣጤ አመጡለት "ለመብሌ ሐሞት ለጥሜ ሆምጣጤን አጠጡኝ ተብሎ የተነገረው ትንቢት በዚህ ተፈጸመ ለታሪኩ ትም ልብስ ሲሆን የአይሁድ ጭፍሮች ልብሱን ገፍፈው ተካፈሉ እርቃኑንም አወጡት ። "ወተካፈሉ አልባስየ ለርዕሶሙ ወተአጸው ዲበ አራዝየ (ልብሶቼን ለራሳቸው ተካፈሉ ፣ በቀሚሴም ላይ እጣ ተጣጣሉ" ሲል ነቢዩ ዳዊት ተናግሮ ነበርና መዝ. ፳፪ ቁ. ፲፰ ።

በግፍ ተነሥተው ይህንን ሁሉ መከራና ስቃይ ሲያደርሱባት አልተቀየማቸውም እንደኃያልነቱም ለጥፋታቸው አላለም ። ከመጠን በላይ ታገሳቸው እንዲያውም "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው " በማለት ወደ ባሕርየ አባቱ ጸለየላቸው ። ይህንንም ከተመለከቱት ብዙዎች እውነተኛ ክርስቶስ መሆኑን አመኑ ፡ በነገሩም አዘኑ ለምሳሌ የመቶ አለቃውና እያለቀሱ ደረታቸውን የደቁ ብዙዎች እንደነበሩ ተጽፎአል ። በግራና በቀኝ ከተሰቀሉትም ወንበዴዎች አንዱ "ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ብሎ በተማፀነ ጊዜ "ዛሬ በገነት ከኔ ጋር እሆናለህ" የሚል የይቅርታ ቃል ሰማ ።

ሌሎች ልባቸው የደነደነ ተመልካቾች ግን ሌሎችን አዳነ ራሱን ለምን አያድንም እያሉ ይዘብቱበት ነበር በግራም የተሰቀለው ወንበዴ አንተ ክስቶስ ከሆንክ አንተም እኛንም አድን እያለ ሲዘብትበት በቀኝ ያለው "አንተ እንዲህ ባለ ፍርድ ላይ ሳለህ እግዚአብሔርን አትፈራውምን ? እኛስ ስለፈጸምነው ወንጀል ይገባናል እርሱ ግን ምንም አላደረገም" በማለት ገሠፀው "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለሚድኑት ግን ኃይል ነው" ተብሏልና ።

ጥፋቱን አምኖ ቅጣቱን የተቀበለና ይቅርታን የጠየቀ ምሕረት ያገኛል ። ፈያታይ ዘየማን የክርስቶስን አዳኝነት አምኖ በመንግሥትህ አስበኝ ብሎ በማጠኑ ወደገነት ለመግባት የመጀመሪያው ሰው ሆናአል ። ነገር ግን ጥፋታቸውን የማያምኑ ፣ በክፉ ሥራቸው የማይጸጸቱ ፣ በሌላው የሚዘብቱ ፣ ሕግን የማያውቁና እግዚአብሔርን የማይፈሩ እንደአብሪተኛው ወምበዴ ፣ ጥፋትን እንጂ ምሕረትን ሞትን እንጂ ሕይወትን የማይሹ መሆናቸውን ከሁለቱ ወንበዴዎች መማር ይጠቅማል ።

በሕግ መተላለፍ ምክንያት በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ በሥጋው አፍርሶ ሰላምን መሠረተልን ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም በሕይወት እንድንኖር በክበረ ደሙ ዋጀን በበደላችንና በኃጢአታችን ሙተን የነበርነውን የሰው ልጆች እግዚአብሔር የምሕረት ባለፀጋ ነውና ሊያድነን ስለወደደ አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮ ሕያዋን አደረገን ከፍቅሩም ብዛት የተነሣ ሞታችንን በልጁ ሞት ለወጠልን "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጠን ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" ዮሐ.፫ ቁ.፲፮ ።

አምላካችን እግዚአብሔር ቁጣው የዘገየ ምሕረቱ የበዛ አምላክ ስለሆነ ይህንን ሁሉ መከራ በትእግሥት አሳልፎ ጠፍተን እንዳንቀር ከባሕረ ኃጢአት አውጥቶ ወደሱ አቅርቦናል ። ስለዚህ በእርሱ አምነናል የምንል ሁሉ በየጊዜው የሚደርስብንን ልዩ ልዩ ፈተና በትዕግሥት አሳልፈን የእርሱን አርአያ በመከተል የሚደርስብንን መከራ ሁሉ በትዕግሥት መቀበል አለብን እርሱም ይህንን ያህል እንደወደደን እኛም ደግሞ በፍጹም እምነት ሆነን በፍጹም ልብ እሱን መውደድ አለብን

ፍቅራችንም በሐሳብና በአፍ ብቻ ሳይሆን ከልብ የመነጨ በተግባር የተገለጠ በመከራ የተፈተነ መሆን አለበት ሕጉን የምናከብር በትእዛዙ የምንመራ ፣ በፍቅርና በአንድነት የጸናን ሆነን ፣ ለእኛ ሲል በመስቀል ላይ የተቀበላቸውን ጸዋትወ መከራዎች ዘወትር እያሰብን እውነተኛ ክርስቲያናዊ ኑሮን መኖር ይገባናል ።

መ/ መንክር ዋሴ

# ከቋጥኝ የተሠራው የኮሬብ ቤተ መቅደስ ታሪክ ፤

በወሎ ክፍለ ሀገር ተንታ አውራጃ መቅደላ ወረዳ ኮሬብ ከሚባል ቦታ ንጉሥ ላሊበላ ያነፀው ቤተ መቅደስ ይገኛል ። ንጉሥ ላሊበላ በ12ኛው መቶ ዓ/ም ላይ የዝቋላን ገዳም ገድሞ የአዳዬ ማርያምን ቤተ መቅደስ አንፆ ሲመለስ ኮሬብ ከተባለው ቦታ ላይ ፣ መቅደስ ፣ ቅድስት ቅኔ ማኅሌት ከአንድ ወጥ ድንጋይ ፈልፍሎና ቦርቡሮ በሚያስደንቅ ሁናቴ ላይ አንፆ ታቦተ ጊዮርጊስን አስገብቶ ቅዳሴ ቤቱን በማክበር ለቤተ ክርስቲያኑ ብዙ መተዳደሪያ ሰጥቶ ወደ ሮሐቤተ መንግሥቱ ተመልሷል ።

በዚህ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም በተሰየመው ቤተ መቅደስ ሲቀደስበት የእግዚአብሔር አምልኮት ሲፈጸምበት እስከ አፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ከቆየ በኋላ ግራኝ መሐመድ ተነሥቶ ከዓፄ ልብነ ድንግል ጋር ጦርነት አድርጎ ድል ካገኘ በኋላ ከዚህ ኮሬብ ከሚባለው ቤተ መቅደስ ብዙ ዕቃ የሚሠውር ዋሻ አለ ሲሉ ስለሰማ ገሥግሶ ከቦታው ሲደርስ ካህናቱ የቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት ከንዋየ ቅድሳት ጋር ሸሽገው ስለአስቀመጡት ምንም ሳያገኝ ቀረ ።

ከቤተ መቅደሱ ቢገባና ቢመለከት የሚያስደንቅ ሰፊ ዋሻ ሁኖ አገኘው በየአውራጃው የዘረፈውን ዕቃ ሁሉ አስገብቶ አስቀመጠበት ። ወዲያው እሳት እንዴት እንደተነሳ ሳይታወቅ በቤተ መቅደሱ የነበረው የግራኝ መሐመድ ከምችት ንብረት ተቃጠለ ። የአገሬው ሕዝብ አጠፋለሁ ብሎ ሲነሣ የዓፄ ልብነ ድንግል ጦር ስለደረሰበት ሸሽቶ ወደ ሌላ አውራጃ ሄደ ።

ግራኝ መሐመድ ድል ከሆነ በኋላ የቅዱስ ጊዮርጊስን ጽላት (ታቦት) ከሠወሩበት ዋሻ ቢገቡ ነብር ዘበኛ ሁኖ አላስገባም አላቸው ። የአካባቢው ሕዝብ ተባብሮ ነብሩን ከአባረረ በኋላ ታቦቱን ለማውጣት የታሸገውን ዋሻ ቢከፍቱ ነዋየ ቅድሳቱ ሲገኝ ታቦቱ ሳይገኝ ቀረ ።

በእኛ አስተያየት እግዚአብሔርን በጸሎትና በምህላ ጠይቀው በሰበካው የሚገኙት የክርስትና እምነት ያላቸው ምእመናን በዋሻው እየገቡ ቢጸልዩበት መልካም ነው እንላለን ።

ደግሞ የሚገርማችሁ በአካባቢው በጉጀ ቅልስ የሚኖሩ ጓጥ ጊዮርጊስ ፣ ደብረ ሲና ማርያም ማታ ሜዳ ቂርቆስ ጨፈርቆ ሚካኤል የሚባሉ ቤተ መቅደሶች ይገኛሉ ። እነዚህም ወደዚህ ቋጥኝ ቤተ መቅደስ ገብተው መንፈሳዊ አገልግሎት ቢሰጥባቸው አንድ አስተያየት ነበር እነዚህን የመሰሉ ሌሎች ብዙ አስደናቂዎች የሆኑ የቋጥኝ ቤተ መቅደሶች የሚንከባከባቸው አጥተው እንደሚገኙም ግልጽ ነው ።

እንግዲህ ኢትዮጵያ ሀገራችን በቋጥኝ ቤተ መቅደስ ሥራ ልትኮራ ይገባታል ምእመናንም በዚህ ሊመኩና ሊኮሩ ይገባቸዋል ።

ከላይ በርእሱ ላይ የገለጽንላችሁን የቋጥኝ ቤተ መቅደስ ጐበኙ በአጋጣሚም ጀግናው ዓፄ ቴዎድሮስ የሞቱበትን የመቅደላን አንባ ታያላችሁ ።

የታሪኩ አቅራቢ
አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ
ዘገነተ ማርያም



www.ethiopianorthodox.org

## ማህበራዊ ኑሮአችን

ከዚህ ቀደም ባርባራ አር ቶምሶንና ፕሮፌሰሩ በከፈቱት የመወያያ መድረክ ተንስተን አልኮል በጤና ፣ በኢኮኖሚ በገንዘብ በአእምሮ መደንዘዝ በስነ ልቡና መረበሽ ላይ የሚያበራክተው ድርሻ እንኳንስ በቃላት ሊገለፅ በአሃዛዊ መረጃ እንኳን ሊዘረዘር እንደማይቻል ጠቅለል ባለ መልክ ማውሳታችን ይታወሳል ኢያሴ የጤና ጠበብት በምርምር እንደደረሱበት አልኮል ከፍተኛ የሆነ የመንፈስ ችግርም የሚያስከትል ነው የዓለም ጤና ጥበቃ ልሳን የሆነው ወርልድ ሔልዝ መጋዚን እንደገለፀው የአልኮል ሱሰኞች ከአላማቸው የተሰናከሉና አቅማቸው የድካም አስተሳሰባቸው የላሸቀና በተለዩም የማየት ችግር የሚቀንስባቸው ዘወትር ሰላምና እረፍት የማያገኙ ቀንም ሌትም መያዣ መጨበጫ በሌለው ቅዠት የተጠመዱ እንደሆኑ በሰፊው አብራርቷል ። ይኸው ጥናታዊ ፅሑፍ የአልኮል ሱሰኞች በዚህ ብቻ አልተወሰኑም ይላል ለጊዜውም ቢሆን አዕምሮን የማነቃቃትና የመቀስቀስ ኃይል ስላለው ወደ በለጠ ጥፋትና የመከራ አዘቅት ወርውሮ የሚጥል በመሆኑ የጠጪዎች ሕሊና መጠነኛም ቢሆን የማስተዋል ዝንባሌ ስለማይታይበት ወደ አመንዝራዎች ወጥመድ የሚያስገባውን መንገድ ይጠርጋል ።

ምንዝርነት የሚያመጣው የበሽታ ናዳ ደግሞ ለመቋቋም የከበደ እንደሚሆን የታመነ ነው ። እንግዲህ መጠጥ ልክ ከሌለው የኅጂነት ባህርይው ሰፍቶ ፀረ ስብዕና አቋም ይይዛል ከአንድ ጥንታዊነት ካለው ታሪካዊ ጽሑፍ እንዳገኘነው የሮማውያን ጣኦት አምላኪዎች መጠጥና ዝሙት አማልዕክቶቻችንን የሚያስደስቱ በመሆናቸው ሁላችንም እነዚህን ተግባራት ማከናወን ይኖርብናል ። እያሉ ተከታዩቻቸውን ከጥፋት ረግረግ ውስጥ ይጨምሩ እንደነበር ይህ ታሪካዊ ፅሑፍ ይገልፃል በስም ያልተጠቀሱ አንዱ የጣኦት ካህን በምስክርበት ጊዜ ከአምላኬ ጋር እገናኛለሁ ። አምላኬ ከፊቴ ቆሞ ንፁሁ ልጄ አንተ ነህ ጻድቅ መሆንህን በምድር እያለህ አረጋግጥልሀለሁ እያለ ሲመሰክርልኝ ያድራል ብሏል ።

ይህ እንኳን ሊበሉት የፈለጉትን አባጉሜ ዥግራ አሉት ከሚለው የአበው ምሳሌ ጋር የሚቀራረብ ይመስለናል ። የጣኦቱ ካህን የመጠጥ ፍቅር ስለደረሰባቸውና አዕምሮአቸው በአልኮል ስለናወዘ አብዝተው የተለማመዱትን የአልኮል መጠጥ እሬትነቱን በቃላት ማርሸፍነው ለማቅረብ ካልሆነ በስተቀርበኛ በኩል ዋጋ የሌለው ነገር ነው ምክንያቱም አልኮል ከልክ ካለፈ አንጀትጉበትን አቃጥሎ ልብን አድክሞ ባጭር ጊዜ የሕይወት መቅሰፍትን የሚያስከትል በመሆኑ መጠጥ እንኳንስ ለፅድቅ ለኃጢአትም አይበጅም እንላለን ነገር ግን እነዛ ጣኦትን የሚያመልኩ ጥንታውያን የሮማ ሰዎች ወደ ቤተ መቅደሶቻቸው መስዋዕትና ስጦታ ለማስገባት ሲሉ ነው ።

እዚህ ላይ መንፈስ የሚለው ቃል ሁለት ትርጉሞችን ይዞ እናገኘዋለን ሣይንሳዊው የመንፈስ ትርጉም ሞራልን ፣ ትህትናን ፣ ክብረ ስብዕናን ፣ ትዕግሥትን ፣ ማስታዋልን ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ነገሮችን ይይዛል ። ሃይማኖታዊ ትርጉሙ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው ይኸውም ከነፍስ ጋራ የተያያዘ ሲሆን ፍቅረ እግዚአብሔርን የፅድቅና የኩነኔ ሐሣብን

እምነትን የመንግሥተ ሰማያት ምኞትን ወዘተ የመሣሠሉትን ያጠቃልላል ስለሆነም መጠጥ ከላይ የተጠቀሱትን ማለትም ሁለቱ የመንፈስ ትርጉሞችን በጋራ የሚያውክ ነው ። በዚህ ምድር ሳለን የሚኖረን መንፈሳዊ ስነ ምግባር አልኮል አዘውትረን የምንጠጣ ከሆን መንፈሳዊ ብቃታችንን እናበላሻለን ማለት ነው ። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ተቃራኒው ይሆናል ። ማለትም አታድርግ የተባለውን ትዕዛዝ መጠጥ ገፋፍቶን እንፈፅመውና በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ ፣ ፍርድ እንዲጠብቀን ይሆናል ። በሌላ ጎኑ ደግሞ ከስብዕናችን ጋራ ግንኙነት ያለውን መንፈሳዊ ትርጉም እናጣለን ። ይህም ማለት በሰላም ፈንታ ጠብና ጭቅጭቅ ፣ በትህትና ፈንታ ግንአህሎኝነት ፣ በትዕግሥት ፈንታ ንዴትና ብስጭትና በመጠጥ ምክንያት ፈጥረን የሌሎችን ሰላማዊ ኑሮ ከማደፍረሳችንም በላይ በጓደኞቻችንና በወዳጆቻችን እምነት እናጣለን ።

ሰብአ ትካት (በኖህ ዘመን የነበሩ ሰዎች ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ጋር ከጠሉዋቸው የኃጢአት ፍሬዎች መካከል አንዱ መጠጥ ለመሆኑ አያጠራጥርም ። ለዚህ የተሰጣቸው ቅጣትም እስከመጨረሻ በጥፋት ውሃ መደምሰስ ሆነ

ስለ መጠጥ ያለንን ግንዛቤ ከአካባቢያችን ጋር ብናዘምደው ብዙ ሰዎች በገንዘባቸው ጠላት ገዝተው በመጠጥ ኃይል ደክመው መንፈሳዊ ምግባራቸውን አቆሽሸው ክብረ ሰብዕናቸውን አበላሽተው በአካባቢያቸው ሕብረተሰብ ተጠልተውና ተንቀው እናገኛቸዋለን ይህም በምሳሌ ብናብራራው አይ እገሌ ጎበዝ ነበር ምሁር እኮ ነው እንዲያውስ ሕሱን ያህል ሊቅ የት አለና? እየተባለ የሚደነቁ አንዳንድ ሰዎች አሉ እንበል ይህ አድናቆት የተሰጠው ሰው የአልኮል ሱሰኛ ሆኖ ዘወትር የሚሰክር ይሆናልና ታዲያ ምን ያደርጋል የሊቅ ደቂቅ ነው ጠጭ በመሆኑ ክብሩን አይጠብቅም የሚል አስተያየት ከሌለው አድማጭ ሲሰነዘርበት ሰውየው የተሟላ ነው ለማለት አጠራጣሪ ወደ መሆኑ ደረጃ እንደርሳለን መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት ሙሉ በሙሉ መጠጥን አያወግዝም ። እንደኛ አስተሳሰብ አንጠጣ ሳይሆን መጠንና ልክ እንወቅ የሚል ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ሲጠራ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ እንደለወጠው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ቃሉም እንዲህ የሚል ነው አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንፃት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር ። እያንዳንዳቸው ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር ኢየሱስም ጋኖቹን ውሃ ሙሉአቸው አላቸው እስከ አፋቸው ሞሉአቸው አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው ሰጡትም አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደመጣ አላወቀም ውሃውንም የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር አሳዳሪውም ሙሽራውን ጠርቶ ፦ ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን ጠጅ ያቀርባል ከሰከሩም በኋላ መናኛውን አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው ። የዮ. ወንጌል ም. ፪ ከቁ ፮-፲፩

ከዚህ የምናገኘው ትልቅ ቁም ነገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ ሲለውጠው ያ ወይን ጠጅ የማያሰክርና የሚጣፍጥ እንዲሁም የሚያስደስት እንደ ነበረ ነው እኛም ህሊናችንን የማይነካ የሚጣፍጥና የሚያስደስት መጠጥ በመጠንና በልክ ብንጠጣ ኃጢአት አይሆንብንም ። ነገር ግን ናላችን በመጠጥ ዞሮ በአካባቢያችን የሚገኙትን ሰዎች ብናስቀይም ትልቅ ኃጢአት በገንዘባችን ገዝተን ተሸከምን ማለት ነው ። አልኮል ስለሚያበረክተው ማህበራዊ ጠንቅ ከዚህ ቀደም ባቀረብናቸው ማስረጃዎች ለመጠቆም ሞክረናል ። ስለሆነም ይህን የአልኮል መጠጥ ርዕስ በዚሁ ላይ እናብቃና በሌላ የማህበራዊ ችግር በሚቀጥለው ጽሑፍ እንገናኝ ።

ቀለመወርቅ መአሾ

## የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ስለሰብአዊ መብት

እንደ ጎርጎሪሳዊው ቀመር ከጥር 16-24 ቀን 1987 በተደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ፣ ስለደቡብ አፍሪካ ጊዜያዊ ተጨባጭ ሁኔታ የቀረበ ማስታወሽ ፤

ሀ/ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የወታደሩ ክፍል ሥልጣን መጨበጥ ፣

ብዙ የፖለቲካ ታዛቢዎች እንዳጤኑት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የወታደሩ ክፍል ሥልጣን መያዝ ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን ለመገምገም ችለዋል ።

የደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት የሰዊቶን አመጽ ፲ኛ ዓመት በዓል ምክንያት በማድረግ ብጥብጥ ይነሣል ብሎ በመፍራት የተቀነባበረ የፀጥታ ኮሚቴ ጥቁሮች በሚኖሩበት ከተማዎች ውስጥ አስቸኳይ አዋጅ በሚል ሽፋን አቋቁሞ ነበር ።

የዚህም ኮሚቴ የበላይ ተቆጣጣሪ የሚሊተሪው ክፍል እንዲሆን ተደርጎ ነበር ። በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛውና ወሳኝ ሥልጣን ያለው አካል የመንግሥቱ የፀጥታው ካውንስል ሲሆን ፣ ይህም የሚያቅፈው የመንግሥት የፀጥታ ካውንስል የወታደሩን ክፍልና ከፀጥታው ክፍል የመረጃውን የበላይ መኮንኖች ይይዛል ።

በመስተዳድሩ ሥር የነበሩት መዋቅሮች ማለትም የአካባቢ ክፍሎች ሥልጣናቸው እየተዳከመ መሄድ ለፖሊሱ ክፍል የአስተዳደሩን ሥልጣን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ አመቺ ሁኔታን እንዲፈጠር በማድረግ ረድቶታል ። የዘረኛው መንግሥቱም ለአንድየና ለመጨረሻ ጊዜ ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ የበላይነቱን ይዞ ለመቆየት ወታደሮቹን በከተሞችና በትምህርት ቤቶች አካባቢ አፍነው እንዲይዙ ሙከራ አድርጎ ነበር ።

ነፍስ ገዳዮችንና (አስኳድስ) ተባባሪዎቻቸው የዘረኛው መንግሥት ተቃዋሚዎች በመምሰል የሚጠራጠራቸውን የጥቁር አፍሪካውያንን መኖሪያ ቤቶችንና ሀብታቸውን በመዝረፍ የውንብድና ተግባር እንዲካሄድ አድርጓል ።

እ.ጎ.ቁ. በአለፈው ታህሣሥ ፲፱፻፹፱ በገና በዓል ሰሞን ፕሮዝዳንት ቦታ የአመፅ ግድያ ከአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ ለመከላከል በሚል ሽፋን ከአሁን ቀደም አውጥቶአቸው የነበሩትን ደንቦችና አንቀጾችን እንደገና በበለጠ እንዲጠናከሩ አድርጓል ።

እ.ጎ.ቁ. እስካለፈው ሰኔ እ.አ.ዘ. 1986 ዓ/ም ቁጥሩ 40.000-80.000 የሚገመት ሕዝብ የጠፉበት ወይም የደረሱበት ያልታወቁ መሆኑ ተረጋግጧል ።

ለ/ ግርፋት ፣ እሥራት ፣ ግድያ ፣

ቀድሞም በተመጣጠነ ምግብ እጦት በተጎሳቆሉት መጠለያ ቤቶቹ የሚኖሩት ጥቁር አፍሪካውያን ወጣቶችና ሕፃናት በተለይ ለዚህ ዓይነቱ አሰቃቂ የግፍ ጭቆናና ግድያ የተለዩ ኢላማዎች ሁነዋል ።

እ.ጎ.ቁ. እስካለፈው ሰኔ አጋማሽ 1986 ዓ/ም ቁጥራቸው ወደ 8000 የሚጠኑ ወጣቶችና ሕፃናት በእሥር ላይ ይገኙ እንደነበር ማስታወሻው በተጨማሪ ያረጋግጣል ።

ከዚህ ውስጥ ግማሾቹ እስካሁን በዚያው ባሉበት እሥር ቤት ሲማቅቁ ይገኛሉ ። ከነዚህ በእሥር ላይ ከሚገኙት 40% ከሚሆኑት ዕድሜአቸው በ11/በ18 ዓመት መካከል የሚገኝ ነው ።

ከታሰሩት ውስጥ በተገኘው መረጃ መሠረት ከእነዚህ ወጣቶች አብዛኛዎቹ በሚያሰቃይ ኤሌክትሪክ ግርፋት በመሰቃየት የሚገኙ መሆናቸው ታውቋል ።

የግፈኛው መንግሥት ይህን የሚያደርግበት ዋና ምክንያት ወጣቶች ያላቸውን አቋምና ሞራል ዝቅ እንዲያደርጉና ራሳቸውን እንዲጥሉ ለማድረግ ሆን ብሎ ታስቦ የተዘጋጀ ዘዴ ነው ።

እንደ ቀመረ ጎርጎሪሳውያን አቆጣጠር በ1986 የደቡብ አፍሪካ ሁለተኛ ከተማ በሆነችው ኬፕታውን ውስጥ በተገኘው የሕክምና ዘገባ መሠረት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሕዝቦች በ1985 ዓ/ም የሞት ቅጣት የተፈጸመባቸው ፊት ለ





www.ethiopianorthodox.org

ፊት ሳይሆን ከበስተጀርባቸው በኩል ነበር ። ከነዚህ ከተረሸኑት ሕዝቦች መካከል በዕድሜ አነስተኛ ሆኖ የሚገኘው የሰባት ዓመት ልጅ ነበር ። በተጨማሪም ከሞት ከተረፉት ከወጣቱ ክፍል አብዛኛው የዘረኛውን መንግሥት አገዛዝ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት እንዲከተሉ ወደሚደረግበት ከኛ ይላካሉ ። የዚህም ዋና ዓላማ ወጣቶቹ በዘር መድልዎው መንግሥት ላይ የሚያደርጉትን ትግል እንዲያጨልመው ለማድረግ ነበር ።

የዚህ ዓይነቱ የግፍ እገዳደል በደቡብ አፍሪካ መንግሥት ላይ ዓለም አቀፍ ቁጣን እያስከተለ ሄዷል ።

በዓለም አቀፍ ዘንድ በታጋይነታቸው የታወቁት ሊቀ ጳጳስ ዴስሞንድ ቱቶ ይህን ጉዳይ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ ግልጽ አድርገው አስረድተዋል ።

እ.ጎ.ቀ. በ1986 የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ ይህን ጉዳይ አስመልክተው ይህ ጭካኔና ኢሰብአዊ ድርጊት እንዲቆም አንድ ጠንካራ መግለጫ አውጥተው ነበር ።

ሐ/ የሕዝብ መገናኛ ሳንሱር ፤

በአሁኑ ጊዜ ሌላው ደቡብ አፍሪካ የዓለም ሕዝብ ጆሮ የሳበው በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኘው ማንኛውም ጥቁሮችን የሚመለከት ዜና ጥብቅ በሆነ ሳንሱር የማለፍ ጉዳይ ነው ። ማንኛውም የዕለት ዜና ወይም ዜናዎቹን የሚመለከት ጉዳይ ሁሉ በማስታወቂያ ሚኒስቴሩ ሳንሱር እያደረገ ከማሳለፉም በላይ ማንኛውም ቴሌቪዥን ካሜራ አንሺዎችና ጋዜጦች በከተሞች ውስጥና ከከተሞችም ውጪ ችግርና ብጥብጥ ባሰጋቸው ቦታዎችና አካባቢዎች ያለ ደቡብ አፍሪካ መንግሥት ፈቃድ የወታደሩንና የፖሊሱን እንቅስቃሴ ወይም ድርጊት ሪፖርት ማድረግ አጥብቆ የተከለከለ ነው ።

ማንኛውም ሕዝባዊ አመጽ እሥራት ወይም የፀጥታ ጉዳዩን በጋዜጣም ሆነ በመጽሔት ማውጣት አጥብቆ የተከለከለ ነው ።

መ/ የሕዝቡ ስሜት ለዚህ ዓይነቱ አዝማሚያ የሚያደርገው ምላሽ ፤

በአሁኑ ወቅት በደቡብ አፍሪካ የጥቁሮች ሠፈር ወይም ከተሞች ውስጥ አንድ ትልቅ ለውጥ እየተከሰተ በመሄድ ላይ ይገኛል ።

የዘረኛው መንግሥት የሥልጣን መድከም የአስተዳደሩ ቁጥጥር እየላላ የበላይነቱን ሥልጣን እያጣ በመሄድ ላይ ነው ። ይህም ሊሆን የቻለው ፦

- የወጣቱ የተዋጊነትና የአልበገር ባይነት መንፈስ ወይም ታክቲክ ጠንካራ በመሆኑ ፤

- የደቡብ አፍሪካ መንግሥት አማካሪዎችና ጥቁር ፖሊሶችን ሊቋቋማቸው ወይም ሊዋጋቸው ባለመቻሉ ፤

ስለዚህ በአሁኑ ወቅት በጥቁር አፍሪካውያን ሠፈሮችና ከተሞች አንድ ትልቅ ኃይል እየተከሰተ ሄዷል ፤ ይኸውም ፦

ጥቁር አፍሪካውያን የራሳቸውን የአካባቢ ፀጥታ አስከባሪዎችና የመንገድ ሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪዎች በመመሥረትና ቀድሞ የነበረውን የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ካውንስል እየተባለ ይጠራ የነበረውን እየተኩ መሄዳቸው ነው።

ለምሳሌ ፤

- መንገድ ማደስን
- የተበላሹ መብራቶችን መጠገንን
- የመንገዶችን ጽዳት መጠበቅን
- በጠቅላላ ቀድሞ ማዘጋጃ ቤቱ ይሠራቸው የነበሩትን ሥራዎች ሁሉ በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል ይገኛሉ ።
- በተጨማሪም በቤተሰብ መካከል የሚነሳውን አለመግባባትን በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ መፈለግ ፤
- እንዲሁም በእሥራት ላይ ለሚገኙ ጥቁር አፍሪካውያን አስፈላጊውን ዕርዳታና እንክብካቤ ማድረግን ያጠቃልላል ።

በተጨማሪም በዘረኛው መንግሥት ቁጥጥር ሥርና የሱ ደጋፊዎች በሆኑት ክፍሎች ለሚከራዩ ቤቶች ኪራይ አለመክፈልን እንዲሁም በመንግሥትና የሱ ደጋፊዎች በሆኑት ሱቆች ውስጥ ገብቶ ዕቃ አለመግዛትን ይጨምራል ።

- በአሁኑ ወቅት በጥቁር አፍሪካውያን ሠፈሮችና ከተሞች ውስጥ አመጽ አስከፊ ገጽታ ላይ ደርሷል ።

በአንፃሩም አድርባይ የሆኑት የጥቁር ቅጥር ወታደሮች የዘረኛውን መንግሥት ተቃዋሚዎች ማለትም ጥቁር አፍሪካውያንን በመግደልና ይህም አድራጎታቸው በጥቁር አፍሪካውያን ወንድሞቻቸው ዘንድ እንዳይታወቅባቸው የጦሩን ክፍል አንድም እንዲደግፋቸው ወይም አይተው እንዳላዩ እንዳያልፏቸው በማድረግ ላይ ይገኛሉ ። ስለዚህ ጉዳይ ብዙዎቹ የጥቁር አፍሪካውያን መሪዎች የአፍሪካን ብሔራዊ ኮንግረስ ፕሬዚዳንት ኦሊቨር ታምቦን ጨምሮ ይህ ከላይ የተጠቀሰው ድርጊት በሕዝቡ አንድነትና ነፃነት ላይ አስከፊ የሆነ መከፋፈል እንዳያመጣ በማለት ያላቸውን ቅሬታ ገልጸዋል ።

ምንም እንኳን ይህ አስከፊ ሁኔታ ቢፈጠርም የዘር መድልዎው ተቃውሞ በጥቁር አፍሪካውያን ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ዘንድ ተቀባይነትን እያገኘ በመሄድ ላይ ነው ።

ለምሳሌ ፤ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ነዋሪ የሆኑት ሕንዳውያን ክልሶችና ከነጮችም ሳይቀር በዘረኛው መንግሥት ላይ ተቃውሞአቸውን እየጨመሩ ሄደዋል ። በተጨማሪም በዚህ ተቃውሞ ውስጥ የሚከተሉት ድርጅቶችና ማኅበራት ይገኛሉ ።

- የደቡብ አፍሪካ ኮንግረስ የሙያ ማኅበራት
- የደቡብ አፍሪካ አንድነት ኮንግረስ
- የአዛቴያን ኮንግረስ የሙያ ማኅበራት

እነዚህ የሙያ ማኅበራት የተመሠረቱት እ.ጎ.ቀ. ታህሣሥ 1985 እና ጥቅምት 1986 ዓ/ም ነው ። የነዚህ የሙያ ማኅበራት ጠቅላላ ቁጥር ወደ 800.000 ይጠጋል ። እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ለትግሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናቸው ። ይህንንም በሚመለከት አንድ ታዋቂ የሆነ ደኩሜንት (ጽሑፍ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቋንቋ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ሰባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቍ.
የመልእክት ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org